# አጋንንቶች፡ በሥጋዊው አድማስ

አሁን እኔ... ? ... [ቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] መስክ ላይ ከወጣሁ ጀምሮ በየትኛውም ስብሰባዎቼ ላይ እንዲህ ሳደርግ ይህ የመጀመሪያዬ ነው። ይህ አዲስ ጊዜ ነው። ወንድም ባክስተር ሄዷል፥ ወ—ወንድም ቦስዎርዝም በህንድ፡ ወይም፡ በአፍሪካ ነው፥ ወንድም ባክስተርም፡ የት እንዳለ አላውቅም። የሆነ ቦታ ሄዷል፡ የቀሩትም ወጥተው ሄደዋል። እኔና ቢሊ እዚህ ቀረን፡ እኛም ጥሩ ጊዜ እያሳለፍን ነው፡ ብቻ መነሳት፡ ማዘጋጀትና መብላት ነው። ስለዚህ፡ እ—እንደዚህ ምናልባት በጌታ እርዳታ፡ እንደዚህ ከቻልን፡ ስብሰባውን በራሳችን፡ ማካሄድ እንደምንችል ይሰማናል። ለዚያም ነው፡ በዚህ ምክንያት ትንሽ ሲካሄድ በማየቴ ደስ የሚለኝ። ጌታ ይህን እንድናደርግ እንደሚረዳን አምናለሁ። አሁን፡ እንደሚታውቁት...

አስተዳዳሪዎቼን እወዳቸዋለሁ። ቦስዎርዝ፡ ባክስተር፡ ሊንዚ፡ ሙር፡ የሚባሉ ግሩም ወንድሞች አሉኝ፡ ባሮኑ ቮን ብሎምበርግን ጨምሮ፡ ሁሉም፡ አምስት ናቸው። በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው። ሰዎች አንድ ነገር ላይ ሰብሰብ ሲሉ፡ ሁሌም እንከን አይጠፋም፡ አንደኛው ያ፡ ሌላኛውም ይህ ይላል። አንዳንድ ጊዜ ይህ እኔ ራሴ ከማስበው ይቃረንብኛል። ስ—ስለዚህ እ—አሁን ነጻ እንደሆንኩ ይሰማኛል። በቃ ትልቅ ጊዜ ማሳለፍ እንችላለን፡ ዝም ብለን እጅጌአችንን ጠቅልለን፡ ገብተን መብላት ብቻ ነው። እጀታችሁን ጠቅልላችሁ ጥ—ጥሩ ጊዜ እንድታሳልፉ እሰባለሁ።

የመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱሴ ተፈጥሮ ነበር። ስለ እግዚአብሔር የተማርኩት ከተፈጥሮ ነው። ዓሣ ማጥመድ እወዳለሁ። ዓሣ ማጥመድ በጣም እወዳለሁ! ልጄ፡ አንተም ዓሣ ማጥመድ ትወዳለህ? ዓሣ ማጥመድ የምትወድ ከሆነ፡ እናትህንም የምትወድ ከሆነ፡ ጥሩ ልጅ ትሆናለህ። ጌታን ማመኔ እንኳ ያንን ነገር ከውስጤ አልወሰደብኝም። ስለዚህ አንድ ቀን ዓሣ በማጥመድ፡ ተራሮች ላይ ነበርኩ። እንግዲህ፡ ይሄን ህጻን ልጅ ለመጥቀም ብዬ ነው። በዚያ በተራሮች ላይ ዓሣ እያጠመድኩ ነበር... በርግጥ፡ እዚህ ቁጭ ብለው ላሉ፡ ለሌሎች ልጆችም ጭምር ነው። እና ትራውት የሚባል አሳ እያጠመድኩ ነበር። እና፡ ኦህ፡ ግሩም የፀደይ ወቅት ነበር። እኔ ልክ እንደዚህ እየሄድኩ፡ በሚቀጥለውም ጉድጓድ ውስጥ ትራውት አሳ ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ ልክ እንደዚያ። ብቻ ጌታን እያመሰገንኩ እየጮህኩ፡ ጥሩ ጊዜ አሳለፍኩ። አንዳንድ ጊዜ፡ ድንበሬን ዝቅ አደርጋለሁ። በመጮኽ አምናለሁ። አሜን። በእርግጥ አምናለሁ። ምክንያቱም፡ አንድ ነገር እንደያዘኝና፡ የሆነ ነገር እንደሚያደርገኝ አውቃለሁ።

2 ስለዚህ ያን ቀን ጠዋት ትንሽ ጠፍቼ ነበር፡ በተመለስኩ ጊዜም፡ በጣም እንግዳው ነገር፡ በሀገሪቱ ውስጥ በኒው ሃምፕሻየር ውስጥ፡ ብዙ ድቦች አሉ። እዚያ ላይ ዓሣ በማጠምድበት፡ ትንሽ ካምፕ አለች። እኔም ትንሽ አሮጌ ድንኳን ተክዬ ነበር፡ የምኖርባት ትንሽ ያረጀች ድንኳን ነበረችኝ። እና ጥቁር ድብ አለ የተባለ በጣም ተንኰለኛ ነገር ነው። ስለዚህ፡ አንድ አሮጊት እናት ድብ እና ሁለት ትናንሽ ልጆቿዋ ወደ ውስጥ ገብተው፡ ድንኳኔን አበላሹ!

3 እሰኪ፡ ከኋላ ባለ ቀይ ፀጉር ትንሿ ልጅ፡ ድቧን ምን ባደርጋት ይሻለኛል፡ ብለሽ ታስብያለሽ? ከኋላ መከተል ነበረብኝ፡ አይደል?

4 እሷ ግን እንዲህ አደረገች። ወደ ውስጥ ገባች፡ ድንኳኔን አፈረሰች እና ሁሉንም ነገር በተነች፡ እዚያም የነበረኝን ምግብ ሁሉ በላች፡ ያንን ሁሉ አድርጋ ተረጋግታ ነበር። ስለዚህ እኔ ሲመጣ፡ ሄደች። ወደ ግልገሎቿ ጮኸች፡ አንደኛው ግልገልም አብሯት ሸሸ። ሌላኛው አይሮጥም ነበር፣ እዚያ ተቀምጦ ነበር። ጀርባውን እንደዚህ፡ ወደ እኔ አዙሮ፡ የሆነ ነገር እያደረገ ነበር። በእጄም ውስጥ ምንም ነገር አልነበረም ነገር ግን ትንሽ ያረጀ መጥረቢያ ነበረኝ። ኢልደር የሚባል እንጨት እቆርጥበታለሁ። መልካም፡ ወደ ሩቅ ቦታ ሮጣ ሄደች፡ ኦህ፡ እዚያ የሰልክ እንጨት ወዳለበት ይመስለኛል፡ እዚያ ተቀመጠችም። ወደ ትንሹ ድብ ጮኸች፡ እርሱም ምንም ትኩረት አልሰጠም። እዚያ መቀመጡን ብቻ ቀጠለ።

5 “ይህ ትንሽ ድብ ምን እያደረገ ነው፡” ብዬ አሰብኩ? ትንሽ ተጠጋሁት። በጣም ለመጠጋት ፈራሁ፡ እንዳትቧጭረኝ ፈራሁ። ስ—ስለዚህ ዛ—ዛፍን ማየት አልቻልኩም፡ እሷም መውጣት እንደምትችል አውቃለሁ። ስለዚህም፡ ወደ እሷ በጣም መቅረብ አልፈለግኩም፡ምክንያቱም የድብ ተፈጥሮን አውቃለሁ። ስለዚህ፡ ትንሽ ተጠጋሁ። ምን እንደተፈጠረ ታውቃላችሁ?

6 አሁን፡ እኔ ፓንኬክን እወዳለሁ። ልጆች ስንቶቻችሁ ፓንኬክ ትወዳላችሁ? ኦህ፡ ቦይ! ኦህ፡ ሽ... ሽማግሌዎችም፡ ጭምር። እጃቸውን ሲያነሱ አይቻለሁ። ሁላችንም ፓንኬኮችን እንወዳለን፡ እኔም እወዳቸዋለሁ፡ በላዩ ላይ ማር ጨምሬ መብላት እወዳለሁ። ባፕቲስት መሆን፡ ታውቃላችሁ፡ ጠበቅ እንድል የሚያደርገን ያ ነው፡ ታውቃላችሁ፡ ማሩ ነው፡ ታውቃላችሁ። ስለዚህም፡ ሰሙኝ፡ በትክክል አጠምቃቸዋለሁ እንጂ፡ አልረጭባቸውም። ጥሩ እና ከበድ ያለውን አይቼ እደፋበታለሁ። እዚህ እና እዚያ ትንሽ አላንጠባጥብም። በደንብ እደፋበታለሁ፡ በማር እንዲሞሉ አደርጋለሁ።

7 ከዚያም፡ ታውቃላችሁ፡ እዚያ ላይ አንድ ባልዲ ማር ነበረኝ፡ ግማሽ ጋሎን ባልዲ ማር ነበረኝ። እና ድቦች ማር በጣም ይወዳሉ። ስለዚህ ይህ ትንሽ ድብ ወደ ውስጥ ገብቶ የዛን የማር ባልዲ ክዳኑን አውጥቶ፡ እንደዚህ ተቀምጦ ነበር፡ ያንን ትንሽ የማር ባልዲ በ... በክንዱ ሥር፡ **እንደዚህ** ይዟል። እና እንዴት መብላት እንዳለበት፡ እንደ እናንተ አያውቅም፡ ታውቃላችሁ፡ ስለዚህ ትንሿን እግሩን ወደ ውስጥ ከትቶ **እንዲህ** ይልሳል፡ ይልሳል። እና እኔን ለማየት ዞረ፡ እና ትንንሽ ዓይኖቹ ሁሉ በማር ተጣብቀው ነበር፡ ትንሹ ሆዱ ሁሉ በማር፡ ተሸፍነው ነበር። እጁን ወደ ታች እያስገባ፡ ልክ **እንደዚህ**፡ መላስ በሚችለው አቅም ሁሉ ማር እየላሰ፡ ተቀምጦ ነበር።

8 ኦህ፡ ማይ፡ ስለ ጥንቱ-ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ሰብሰባ ትዝ አለኝ፡ ባልዲውን ስንከፍት፡ እጃችንን ወደ ማሰሮው ውስጥ አስገብተን ስንመለስ። ታውቃላችሁ፡ ደጋግመን፡ እየላስን እንመለሳለን።

9 በጣም አስቂኝ የሆነው ነገር ምን እንደሆነ፡ ታውቃላችሁ? ይህ ትንሽ ድብ የቻለውን ያህል ካገኘ በኋላ፡ ባልዲውን ጥሎ ወደ ውጭ ሮጠ። ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? እናት ድብ እና ሌላኛው ትንሽ ድብ ማሩን ለማግኘት፡ እሱን መላስ ጀመሩ።

10 ስለዚህ፡ መልካም፡ ምናልባትም ስብሰባችን በዚህ መልክ ሊሆን ይችላል ብዬ፡ ተስፋ አደርጋለሁ፡ ስለዚህ ለሌሎችን መናገር እንቀጥላለን፡ የእግዚአብሔርም ክብር በእኛ ላይ ይወድቃል። መልካም።

11 እናንተ ትንሽ ልጆች እናንተን እዚህ በማየቴ ደስ ብሎኛል። እንዲህ ያለ ነገር ለእናንተ መንገር እወዳለው። ምናልባትም ነገ ከሰዓት በኋላ፡ ተጨማሪ ጊዜ አለን፡ እ—እና ትንሽ ተጨማሪ ነገር መነጋገር እንችላለን። እና አሁን ስለ አንድ ነገር ከአባታችን እና ከእናታችን ጋር እንነጋገራለን።

12 ስለ **ስለ አጋንንት** እንነጋገራለን። በመዝሙር 103፡1 እስከ 3፡ ላይ እነዚህን ጥቅሶች እናነባለን። አብዛኞቹ ሁሉም አገልጋዮችና ቀሳውስቶች፡ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢያን፡ በልባቸው ያውቋቸዋል።

> **ነፍሴ ሆይ፡ እግዚአብሔርን ባርኪ፡ አጥንቶቼም ሁሉ፡ የተቀደሰ ስሙን።**
>
> **ነፍሴ ሆይ፡ እግዚአብሔርን ባርኪ፡ ምስጋናውንም** ሁሉ **አትርሺ፡**
>
> **ኃጢአትሽን** ሁሉ **ይቅር** የሚል፣ **ደዌሽንም** ሁሉ **የሚፈውስ፣**

13 እዚህ ላይ "ሁሉ፡" የሚለውን ልብ ብላችሁ እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። "ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፡ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ።" አሁን ለአፍታ ብቻ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

14 አሁን፡ የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ እዚህ ስለመገኘታችን እናመሰግንሃለን። በዙሪያችን ስለተቀመጡት ስለነዚህ ትናንሽ ልጆች እናመሰግንሃለን፡ ኢየሱስ ካልመጣ፡ ነገ የሚኖር ከሆነ፡ የነገ ወንዶችና፡ ሴቶች እነዚህ ናቸው። አሁንም፡ አባት ሆይ፡ አሁን ስ—ስለ ቃልህ እና ስለ ታላቁ ጠላታችን ስለ ሰይጣን፡ እየተነጋገርን ሳለን፡ እንድትባርከን እንጸልያለን። አምላካችን ሆይ፡ በዚህ ምሽት፡ እያንዳንዱ እርምጃውን፡ የሚቋቋመውን፡ የእግዚአብሔርን ኃይል፡ በመጠቀም የፊት የጦር ግንባርን እንድናስቀምጥ እንድታደርገን እንጸልያለን፡ ጌታ ሆይ፡ እርሱንም ምንም ዓይነት ሕጋዊ መብት እንደሌለው፡ ክርስቶስ በእኛ ምትክ በዚያ በቀራንዮ ሲሞት፡ እንዳሸነፈው፡ አለቆችንም አፍርሶ ሰይጣንን የነበረውን ኃይል ሁሉ—ሁሉ እንደዘረፈው አሳየው። አምላካችን ሆይ፡ እንዴት መፈወስ እንደሚቻል፡ እና ሰይጣንን እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻል፡ ለሰዎች እንዴት ማወቅ እና ማስረዳት እንደምንችል አሁን ጥበብን እና ማስተዋልን ስጠን። በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን።

15 አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች **ስለ አጋንንት** እንነጋገራለን። ስለ አጋንንት ብዙ ትሰማላችሁ። አሁን፡ ነገ ከሰዓት በኋላ ምናልባት እንጨርሳለን። ለማንኛውም፡ በዚህ ሳምንት ለሁለት ቀናት፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መስበክ ፈልጌአለሁ… ወይም ደግሞ ለሁለት ቀናት ከሰዓት በኋላ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ፡ ለመናገር ፈልጌአለሁ።

16 አሁን፡ የመጀመሪያው ነገር፡ አጋንንት ምን እንደሆነ ነው። ብዙ ሰዎች ስለ አጋንንት ሲናገሩ ትሰማላችሁ። መልካም፡ አሁን፡ "ጋኔን፡ ዲያብሎስ፡" ሁሉም ከአንድ ቃል የመጣ ነው፡ በእንግሊዝኛ "የሚያሰቃይ" ይባላል። የሚያሰቃይ አካል ዲያብሎስ ነው፡ ክፉ ሰው ነው። እንዲህ ይላል… አሁን፡ ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ፡ ለአብዛኛው ሰው፡ ለብዙ ሰዎች፡ ወንድ እያታቸው እና ሴት እያታቸው

ያነበቡት የድሮ መጽሐፍ፡ ወይም እንደዚህ ያለ ነገር ነው። “በእሱ ውስጥ ብዙ ነገር የለም፡ እሱ ለድሮ ሰዎችና፡ ለመሳሰሉት ነው” ይላሉ። ያ ግን ስሕተት ነው። ለሁሉም ሰው ነው። አጋንንቶች እኛን የሚያሠቃዩ አሰቃዮች ናቸው።

17 አሁን፡ ወደ ሰው ነፍስ የሚገቡ አጋንንቶች አሉ፡ ያም፡ በንግግሩ አጠራር፡ ያ—ያ በ… እኔ ግን፡ ይህን እላለሁ፡ ወደ ነፍስ የሚመጣው ጋኔን ነፍስን የሚያሰቃይ ነገር ነው።

18 ብዙ ጊዜ ምናልባት እብድ ሰው ልታዩ ትችላላችሁ። አሁን፡ ምናልባትኮ የተለወጠ ሰው፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ሊሆኑ ይችላል፡ ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ እብድ ነው። አያችሁ? ያ ትክክል ነው። ይህ ከነፍስ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። የሚያሰቃይ ነው፡ አያችሁ፡ የሆነ የሚያሠቃያቸው ነገር ነው።

19 አሁን፡ ደግሞ ሁሉም በሽታዎች፡ ከዲያብሎስ የመጡ መሆናቸውን ማወቅ አለብን። በሽታን ያመጣው እምላክ አይደለም። በሽታ የሚመጣው ከአምላክ አይደለም። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ታዛዥ ባለመሆናችሁ፡ እንደ ማረሚያ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲመልሳችሁ፡ ሰይጣን በሽታን እንዲያመጣባችሁ ይፈቅድለታል። በሽታ ግን፡ መጀመሪያ ላይ የሚመጣው ከዲያብሎስ ነው። አንድ ሰው በሰማይ የሚኖረው፡ አባታችን የሆነው አምላክ፡ በሽታና ሞትን ያመጣው እርሱ ነው ብሎ ማመን ይችል ይሆን? መልካም፡ አይደለም፡ እርሱ አይደለም፡ ከቶውንም አልነበረም፡ ወደፊትም አይሆንም። አምላክ ታዛዥ ባለመሆናችሁ ምክንያት ሞት እንዲኖር ፈቅዷል። እግዚአብሔር ሞትን ይፈቅዳል። አንድ ጸሐፊ እንደተናገረው፡ “ሞት ሊያደርገው የሚችለውን ሁሉ፡ እግዚአብሔር በጋሪ ላይ አሰሮታልና አማኝ እንድንሆን፡ ወደ እግዚአብሔር ፊት ይጎትተናል።” **ሞት** ማለት ግን “መለየት” ማለት ነው።

20 ኢየሱስም፡ “ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።” እርሱም፡ “ትንሣኤና፡ ሕይወት፡ እኔ ነኝ የሚያምንብኝ፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ይሆናል፡ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም።” እርሰ በርሳችንም ሥጋችንን በቅዱሳን መቃብር ላይ እናከማቻለን። “ለዘላለም ግን አይሞትም።”

21 ሰለ አልዓዛርም ሲናገር ብትመለከቱ፡ “አልዓዛር ተኝቷል፡” አለ።

22 ደቀመዛሙርቱ፡ ልክ እንደ እኛ ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን፡ “ኦህ፡ ተኝቶ ከሆነ መልካም አድርጓል፡” አሉ። “እረፍት መውሰድ ነው፡” ብለው አሰቡ።

23 እሱ ግን መጥቶ በቋንቋቸው አነጋገራቸው። “በምታምኑት ቋንቋ፡ ‘ሞቷል፡’ አላቸው። እኔ ግን፡” አላቸው፡ “እኔ ሄጄ እቀሰቅሰዋለሁ፡ አሰነሣዋለሁ።” አያችሁ? አ… ያችሁ?

24 **ሞት** ማለት “መለየት” ማለት ነው። አሁን፡ ከእናንተ መካከል አንዱ፡ ከቤተሰቦቻችሁ አንድ ሰው፡ ቢሞት፡ ወይም ሌላ ነገር፡ ጌታን የተቀበለ ከነበረ፡ አልሞተም። ከሰብዓዊ አመለካከት አንጻር ሲታይ ሞተዋል። ብቻ ከእኛ ተለይተል፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ ናቸው። ሙታን አይደሉም፡ መሞትም አይችሉም፡ መሞት ለእነሱ የማይቻል ነው። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ “ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድ አይመጣም።” ስለዚህ፡

ሊሞት አይችልም። የማይሞት፡ ዘላለማዊ የሆነ ነገር ሁሉ፡ ሊጠፋ አይችልም። ይህ የማይጠፋ ሕይወት ነው። እግዚአብሔር ስለ ሰጠው አግኝቶታል። እና እ—እንደ ሽልማት አይደለም፣ እሱ ከ... ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ነው። እግዚአብሔር ይሰጠዋል።

25 እግዚአብሔር ይጠራል። እግዚአብሔር ካልጠራው በቀር ማንም ወደ እግዚአብሔር ሊመጣ አይችልም። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "አባቴ ከጠራው፡ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም።" ልክ ነው? ስለዚህ እግዚአብሔር በሁሉ ነው። ምናልባት ነገ ከሰዓት በኋላ ስለዚያ ትንሽ ተጨማሪ ነገር እንነጋገራለን፡ ምክንያቱም ይህን እንድታዩት፡ ይህንን **የበሸታው** ነገር፡ ወደ እናንተ ማድረስ እፈልጋለሁ።

26 በአንድ ጊዜ ቅድመ-አያቶቻችን ውስጥ እንደዘር ተቀምጠን እንደነበርን ታውቃላችሁ። እናንተም ታውቁታላችሁ። ዶክተሩም ያውቀዋል። መልካም፡ እናንተም፡ ታውቁታላችሁ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች። የሕይወት ዘር በቅድመ-አያታችሁ ውስጥ ተጀምሮ፡ ዘር ሆኖ፡ በአያታችሁ በኩል፡ ወደ አባታችሁ፡ ከዚያም ወደ እናታችሁ እና አሁን ወደምትገኙበት ሁኔታ እንደ መጣ ታውቃላችሁ። ያ ትክክል ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት እንኳን ይህንን ያስተምራሉ። ከፈለጋችሁ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅስ ይሄው። ሌዊ ቅድመ-አያት በሆነው በአብርሃም ወገብ ውስጥ በነበረበት ጊዜ፡ አሥራት ከፍሎ እንደነበር ይናገራል። ያ ትክክል ነው? ስለዚህ፡ አያችሁ፡ ዘሩ ወደ ኋላ ይሄዳል።

27 ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ በፈጠረው ጊዜ፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ነፍሶቻችሁ ተፈጥረዋል፡ ይህም የሰው መንፈስ፣ **ሰውን** በሰው መልክ ሳይሆን፡ **ሰውን** በመልኩ። አያችሁ? ከዚያም በምድር ላይ ሰው ከመፈጠሩ በፊት፡ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ዛሬ ከሰዓት በኋላ ጊዜያችንን ወስደን ወደዚያ ለመመለስ፡ ዕድሉ ቢኖረን ምኞታችን ነው። እግዚአብሔር እንዴት... ተመልከቱ፡ አሁን፡ ይህ ማለት በመሰመር ውስጥ ለውስጥ ማለት ነው፡ ነገር ግን፡ ስታዩት፡ በመሰመር ውስጥ ይመጣል። አያችሁ? እግዚአብሔር እንዴት እንደነበር፡ መጀመሪያ ላይ፡ ምን እንዳደረገ፣ እንዴት ወደ ምድር እንደወረደ እና እንዴት ሰውን እንደራሱ ምሰል እንደፈጠረ፡ ከዚያም እግዚአብሔር ወደ ኋላ ዞር ብሎ ሰውን ለመበዝበት፡ በሰው ምሰል ተፈጠረ።

28 አሁን፡ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ሲፈጥረው፡ መንፈሳዊ ሰው ነበር። ከዚያም መሬትን የሚያርስ ሰው አልነበረም። ከዚያም ሰውን ከምድር አፈር ፈጠረው። አሁን፡ ክሮኖሎጂስቶች፡ እና ሌሎች፡ እነዚህ የቅሪተ አካል እና ጥንታዊ አጥንቶች ተመራማሪዎች፡ በመሳሰሉትም፡ በዝግመት ያምናሉ... እኔም በትክክለኛው ዓይነት የዝግመተ ለውጥ አምናለሁ። የሰው መለወጥ ከራሱ ይነሳል፡ ሌሎች ሁሉ ግን ከአንዱ ህዋስ አይደሉም። አይደሉም፡ ወዳጄ፡ ምክንያቱም አምላክ አ—አንድ ወፍ ወፍ አድርጎ ከፈጠረበት ጊዜ አንሥቶ ወፍ ወፍ ነው፡ ዝንጀሮ ዝንጀሮ ነው፡ ሰው ደግሞ ሰው ነው። ትክክል።

29 አሁን፡ በቅርብ ጊዜ እዚህ ሉዊስቪል ውስጥ፡ ከአንድ ሐኪም ጋር እየተነጋገርኩ ነበር። እንዲህ አለኝ፡ "ይኸውልህ፡ ሬቨረንድ ብራንሃም" አለኝ! እኔ ስለ አፍሪካ ተወላጆች እየተናገርኩ ነበር፡ ስለ አመጋገባቸው፡

ስለ አደራረጋቸው... ኦህ፡ ከመቼውም ካያችሁት ነገር ሁሉ አሰቃቂው ነገር፡ አመጋገባቸው! የበሰበሱ ነገሮች ለቃቅመው፡ በውስጡ ትሎች ያሉበትን፡ ትሎች እና በውስጡ ያለውን ያራግፋሉ። ምንም ለውጥ አያመጣም። አ... አያችሁ? ማንኛውንም ነገር ቢጠጡ፡ ምን እንደሆነ ምንም ለውጥ አያመጣም። እንዲህ አለኝ፡ “ነገር ግን፡ ሬቨረንድ ብራንሃም፡ እነዚህ ሰዎች ሰዎች አይደሉም” አለኝ።

እኔም፡ “ኦህ፡ አዎን፡ ሰዎች ናቸው እንጂ። በእርግጥ ሰዎች ናቸው” አልኩት።

30 እንዲህ አልኩት፡ “በአውሬው ዘር ውስጥ፡ ከሰው ጋር በጣም የሚመሳሰለው እንስሳ፡ ቺምፓንዚ ነው። ላለፉት አራት ሺህ ዓመታት ያህል ቺምፓንዚ አንድ የሰው ንግግር ለማናገር ሞክራችኋል፡ አልቻለምም፡” “ምክንያቱም ማሰብ አይችልም። የሚያሰብበት ማሰቢያ የለውም፡” አልኩት። ኦህ፡ እንደ ፈረስ ጊ እና ሃው፡ ወይም መነፅር ማድረግ፡ በትንሹ ልታስተምሩት ትችላላችሁ፡ ወይም ሲጋራ ማጨስ፡ ወይም እራሱን በብስክሌት ላይ ማመጣጠንን፡ ፈረስ መንዳትን፡ ወይም እንደዚህ ያለ ነገሮችን ልታስተምረው ትችላላችሁ፡ ይህ ግን ልክ እንደፈረስ “ጊ” እና “ሃው”፡ ወይም እንደ ውሻ “ዊት፡” የመሳሰሉ ነገሮች ነው። “እንስሳ ነው፡” አልኩት።

31 “ነገር ግን አለ ወደተባለው ብሔረሰብ፡ ወደ ጫካው ሰው፡ ወደ አፍሪካ እንድመለስ ትፈቅድልኛለህ።” እኔም፡ “ምናልባት የእርሱ ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ-ቅድመ አያቱ ነጭ ሰው ወይም ምንም ነገር አይቶ አያውቅም” አልኩት። የሚያውቀው ብቸኛው ነገር፡ ቀኝ እና ግራ እጅ የትኛው እንደሆነ እንኳን አያውቅም። የሚያውቀው ብቸኛው ነገር መብላት ነው፡ በእጁ ማግኘት የሚችለውን ይበላል፡ የሰው ሥጋ ቢሆን፡ ሌላ ማንኛውም ነገር ቢሆን፡ ለእሱ ምንም ልዩነት የለውም፡ ብቻ ይበላዋል። ነገር ግን በአምስት ዓመቱ ልወሰደውና፡ በአሥራ አምስት ዓመቱ ጥሩ እንግሊዘኛ ይናገራል ጥሩ ትምህርትም ይማራል። ለምን? ነፍስ አለው። እግዚአብሔር ሰው አድርጎታል፡ እርሱም እንደ ሌሎቻችን ወንጌልን የመስማት መብት አለው፡ ቢያንስ አንዴ እንኳን፡ በመላ አሜሪካ፡ በዙርያው ሁሉ እንደምናደርገው፡ ደግመን፡ ደግመን ደጋግመን ሰንሰብካቸው፡ ሰንለምናቸው፡ ሰናሳምናቸው እና ሌላው ሁሉ አድርገናል። እስኪ አንድ ጊዜ ይሰማው፡ ከዚያም ሮጦ እየጮኸው በፍጥነት ወደ መሰውያው ካልቀረበ ተመልከት።” አየህ? አዎን፡ ወዳጄ!

32 ዛሬ፡ አፍሪካን ሳሰብ፡ ልቤ እንዲህ ነው፡ ወንድሜ፡ እነዚያም ምስኪን ጥቁር እጆች ሲነሱ፡ እንዲህ ሲሉ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ስለ ኢየሱስ አንድ ተጨማሪ ጊዜ!” አቤቱ፡ ማረን! በውስጤ የሚቆፍር እና የሚቀጣጠል ነገር አለኝ። በቂ ገንዘብ እንዳገኘሁ፡ ወዲያው፡ ወደዚያም እሄዳለሁ። ከምበላው በተጨማሪ፡ በማገኘው በእያንዳንዱ ሳንቲም፡ ሁሉንም ነገር የማደርገው ይህንን ነው፡ እግዚአብሔር ያውቃል። አብዛኞቹ ሰዎች ልብሶቼን ይሰጡኛል። እኔ ራሴ፡ ለመኖር የቻልኩትን ያህል፡ ራሴን ችዬ የምኖርበትን ገንዘብ፡ በቀጥታ መንግሥት ባዘጋጀው በሚሲዮናዊነት ፈንድ ውስጥ አስገባዋለሁ። የገቢ ግብርም እንኳ አልከፍልም። ሦስት ወይም አራት፡ አምስት ሺህ ዶላር ለማግኘት፡ ወደዚያም እሄዳለሁ ወንጌልንም ለሰዎች እሰብካለሁ በዚያ ቀን መልስ መስጠት እንዳለብኝ አውቃለሁ። ምን እንደምመልስም አውቃለሁ።

33 እኔ ወደ አንድ ከተማ ስሄድ፡ ትልቅ ስብሰባ አደርግ ነበር፡ ብዙ ገንዘብ ሲገኝ፡ ታላላቅም ዘመቻዎች እና በሺዎች የሚቈጠሩ ዶላሮች ሲሰበሰብ፡ ለቀይ መስቀል እና ለመሳሰሉት እሰጥ ነበር። አሁን፡ አሁን፡ እነርሱን ለመምታት አይደለም፡ ነገር ግን ትልቅ የአልማዝ ጉትቻ አድርገው አራት-ሺህ-ዶላር መኪና ውስጥ፡ ሲጋራ በማጨስ በመንገድ ላይ እየመጣ፡ በታመሙ ሰዎች፡ ገንዘብ በሳምንት አምስት መቶ ዶላር-... አይደለም፡ ወዳጄ! በእርግጥ፡ አይደለም! በእነዚህም ላይ፡ ከከተማውም እንደወጡ ወዲያውኑ፡ "ሆሊ ሮለሮች፡" ይላሉ፡ እንደዚህ ያሉ ነገሮች ሁሉ፡ መሳለቅ፡ የቆምንበትንም ሃይማኖት ዝቅ ማድረግ። አይደለም፡ ወዳጄ!

34 እኔ ራሴ፡ በእግዚአብሔር ፊት ዳኛዬ አድርጌ እወስዳለሁ፡ ከአድማስ ባሻገር ባለው የወንጌል ሥራ ውስጥ አስቀምጣለሁ፡ ስለዚህ በዚያ ቀን እኔ አውቃለሁ... ስለ አገልግሎቴ ምላሽ መስጠት ሲኖርብኝ፡ ምላሹ ትክክል ይሆናል። ያ በጣም ትክክል ነው፡ ምክንያቱም ሰዎችን ስንከባከብ እግዚአብሄርን እንደምንከባከብ ገብቶኛል። ስለ እናንተ ያለኝ አመለካከት ስለ ክርስቶስ ያለኝ አመለካከት ነው። በእኔም ላይ ያላችሁ አመለካከት ተመሳሳይ ነገር ነው፡ ስለ ክርስቶስ ያላችሁ አመለካከት ነው፡ ይህ ትክክል ነው።

35 አሁን፡ እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ማየት፡ እና እያችሁ እንዴት አንድ የሰው ልጅ፡ ከዚያም፡ የማይሞት ነፍስ ያለው፡ የማይሞት፡ የማይጠፋ፡ የዘላለም ሕይወት ከማግኘት በስተቀር ምንም ማድረግ የማይችል፡ እግዚአብሔር በሉዓላዊነት፡ በራሱ ፈቃድ፡ እንዴት እንደ ሰጣችሁ ተመልከቱ። አሁንም፡ ከዚያ፡ አሁን እኔ...

36 ይህንን ትንሽ ላርመው፡ ወይም አንድ ነገር ልበል። አንድ ሰው ሄዶ፡ "ወንድም ብራንሀም ካልቪኒስት ነው" ሊል ይችላል። አይ፡ አይደለሁም። ካልቪኒስት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እስካለ ድረስ ካልቪኒስት ነኝ። ካልቪኒስት ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲወጣ ግን፡ ያን ጊዜ አርሜኒያን ነኝ፡ እያችሁ። በቅድስና፡ እና በካልቪኒዝም አምናለሁ። ነገር ግን፡ ሁለቱም፡ አንዱ **በዚህ** አቅጣጫ ከመስመሩ ወጥቶ ሄደ፡ ሌላኛው ደግሞ **በዚያ** አቅጣጫ ከመስመሩ ወጥቶ ሄደ። እንግዲህ መልሶ ወደ ቦታው ለመመለስ፡ እግዚአብሔር ባደረገው ትክክለኛ ቦታ ላይ ለማስቀመጥ የኤፌሶን መጽሐፍ ባይኖር ኖሮ፡ ሁላችንም ግራ ተጋብተን ነበር። ነገር ግን ሁለቱም አንድ አስተምህሮ አላቸው፡ እያንዳዳቸው ግን፡ በእሱ ላይ ዘር ለመዝራት ሄዱ፡ ይህም ሆሊነስ እና ካልቪኒስቶች፡ ደግሞም፡ አርሜኒያውያን ናቸው። አሁን፡ ካልቪኒስቶች አንድ እውነት አላቸው። እኔ እ—እንደማምነው የካልቪኒስቶች ትምህርት...

37 እኔ ይህን አምናለሁ። ደኅንነት በተመለከት፡ ቤተ ክርስቲያን ዘላለማዊ ደኅንነት እንዳላት አምናለሁ። መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ማንኛውም ሰው ይህን ያውቃል፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ እንደተናገረው ምንም ነውር በዚያ አያይም። ትክክል ነው? ከዚያም፡ ይህ በዚያ ይሆናል። ያ ትክክል ነው? ቤ-... ቤተክርስቲያን ለዘለዓለም የተጠበቀች ነች። አሁን፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ናችሁ፡ የምለው ቀጣዩ ነገር ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ከሆናችሁ፡ እንግዲህስ፡ ከቤተክርስቲያን ዘንድ ደኅንነት አላችሁ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጽናት ግን አለብህ። ወደ ቤተክርስቲያን የምትገቡት እንዴት ነው? እጅ በማንሳት? አይደለም። ስማችሁን በመፅሃፋ ላይ በማስመዝገብ? አይደለም፡ ወዳጄ። "በአንድ መንፈስ ሁላችንም አንድ

አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።” ያም አካል፡ እግዚአብሔር በቀራንዮ ላይ የፈረደው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ነበር፡ እኛም ወደዚያ አካል በአንድ መንፈስ ተጠምቀናል። በክርስቶስ አካል ውስጥ እስካለን ድረስ ዘላለማዊ ደኅንነት አለን፡ ምንም ነገር ሊለየን፡ ምንም ነገር ሊነካን አይችልም። ወደ ውጭ ከወጣችሁ፡ የምትወጡት በራሳችሁ ፈቃድ ነው። ነገር ግን በእርግጠኝነት፡ በክርስቶስ አካል ውስጥ ከሆናችሁ፡ ኢየሱስ ከሙታን እንደተነሳ፡ እናንተም ትነሳላችሁ። እግዚአብሔር እ... አስቀድሞ ይህን አድርጓል።

38 ኃጢአት መሰራት አትችሉም። ኦህ፡ በ... በዓይናችሁ ፊት ኃጢአተኛ ልሆን እችላለልሁ፡ በክርስቶስ ከሆንኩ ግን፡ እግዚአብሔር ያንን አያይም፡ ምክንያቱም የደሙ ስርየት... ለኃጢአቴ ነው። አያችሁ? ኃጢአት ልሠራ አልችልም። “ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፡ ኃጢአትን ሊያደርግ አይቻለውምና። የእግዚአብሔር ዘር በእርሱ ይኖራልና።” አያችሁ? እሱ፡ እሱ ስሕተት ከሰራ፡ በእርግጥ፡ እሱ ትክክል፡ ከዚያም ለመናዘዝ ፈቃደኛ ይሆናል። እውነተኛ ክርስቲያን ከሆነ፡ ያንን ያደርጋል። ወደኋላ የሚል ከሆነ፡ ከጅምሩ፡ ምንም ነገር እንዳላገኘ ያሳያል። ይህ ትክክል ነው። ገና፡ ምንም ነገር የለውም። እውነተኛ ክርስቲያን ከሆነ ግን...

39 እዚህ ላይ፡ የሰንዴ ቅንጣት መሬት ላይ ብትዘሩ፡ ሁሌም የሰንዴ ቅንጣት ናት። እንክርዳድ እና ሌላም ነገር ሁሉ፡ በዙሪያዋ ሊሆን ይችላል፡ ከበቀለ በኋላ ግን የሰንዴ ቅንጣት መሆኑ የማይቀር ነው። ያ ትክክል ነው? አንድ ሰው በእርግጥ ከእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ ከሆነ፡ ወደ ውስጥ እና ወደ ውጭ፡ እና ወደ ኋላ እና ወደ ፊት፡ እና በዚያኛው ዓለም ውስጥ እና እዚህ ደግሞ ውጭ አይሆንም። አይ፡ ወዳጄ። አይ፡ አይደለም። እናንተ አንድ ቀን እንክርዳድ በሚቀጥለውም ቀን የሰንዴ ቅንጣት አይደላችሁም። እግዚአብሔር በሜዳው ውስጥ ያ የለውም። አዎ፡ ወዳጄ። ከመንፈስ ቅዱስ የተወለዳችሁ ከሆናችሁ፡ ከዚያን ጊዜ እንሥቶ እስከምትሄዱበት ጊ... ጊዜ ድረስ ክርስቲያን ናችሁ፡ ከዚያም ከ—ከእግዚአብሔር ጋር፡ ዘላለማዊ ትሆናላችሁ። በቤተክርስቲያን ውስጥ ካላችሁ፡ ያ ትክክል ነው።

40 አሁን፡ አሁን ስለ ሞት እንነጋገር። አሁን፡ አንድ ሰው በዚያ ርስት ውስጥ ሆኖ፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ፡ ለምን ይታመማል? ምክንያቱም ሰውነታችሁ ገና ስላልተዋጀ ነው። ሰውነታችሁ አልተዋጀም። ምንም ይሁን ምን፡ ምንም ያህል ጥሩ ብትሆን፡ ምንም ያህል ጻድቅ ብትሆን፡ ምንም ያህል ቅዱስ ብትሆን፡ ምንም ያህል መንፈሳዊ ብትሆን፡ በነፍስህ ብቻ ነው። ነፍስህም ገና አድጋ አላለቀችም። ነፍስ ያገኘችው፡ የመዳናችን ዋስትና የሆነውን፡ የገባልንን የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል ብቻ ነው። አሁን ግን የትንሳኤ ዋስትና ከሌለን፡ መለኮታዊ ፈውስ ከሌለን፡ ትንሣኤ እንዳለ የሚያረጋግጥልኝ ዋስትና ወይም ምንም ነገር አይኖረኝም።

41 ልክ ክርስቶስ በልቤ ውስጥ የማይኖር ከሆነ፡ እንግዲህ የተረዳሁት ከአንድ ዓይነት የ—የስነልቦና ነገር የተራድሁት ከሆነ፡ እምነቴ በእንደዚህ አይነት ነገር ከሆነች፡ መልካም፡ እ—እ—እንግዲያውስ ተጠራጣሪ እሆናለሁ። ለዚህም ነው፡ በአፍሪካ፡ በሚስዮናውያን፡ ሲመጡ፡ በሺዎች የሚቈጠሩ የአገሬው ተወላጆችን ይዘው ሲመጡ፡ ትንንሽ የጭቃ ጣዖቶችን እና ሌሎች ነገሮችን ሁሉ ይዘው የመጡት፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በሥነ ልቦናዊ ገጽታው

ስምተውት ስለነበር ነው። ያ ትክክል ነው። የራሴ ቤተክርስቲያን ደግሞ ባፕቲስት፡ ሜቶዲስት፡ ፕሬስባይተሪያን፡ ሁሉም ወደዚያ ገብተዋል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ኃይል በተግባር ሲገለጥ ባዩ ጊዜ፡ ተስተካከሉ፡ ያኔ እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን አወቁ።

42 አሁን፡ ግን፡ በሽታ የሚጀምረው እንዴት ነው? አሁን፡ የመጀመሪያው ነገር፡ በሽታ ከመሆኑ በፊት መንፈስ ነው፡ ልክ አንተ ሰው ከመሆንህ በፊት መንፈስ እንደነበርክ። አሁን እዚህ ወንድም ዊሌትን እንደ ምሳሌ እጠቀማለሁ። ወንድም ዊሌት፡ እ... እኔና አንተ ምንም ያልነበርንበት ጊዜ ነበር። ከዚያም የመጀመሪያው ነገር፡ እግዚአብሔር ሕይወት ሰጠን። እንበልና፡ ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ ሰውነትህን ብወስድ፡ ሰውነትህ የተገነባው፡ በአቶሞች በተያያዙ በብዙ ህዋሶች ነው። አሁንም፡ ኢየሱስ የሚዘገይ ከሆነ፡ አንድ ቀን እነዚህ አቶሞች ይጠፋሉ። ወደ ኋላ ትመለሣለህ። እንደ መጀመሪያው ይሆናሉ፡ ወደ አየር ይመለሳሉ። ነገር ግን መንፈስህ ሲመለስ፡ አተሞቹ ከመንፈስህ ጋር እንደገና ይሰበሰባሉ እናም ልክ እንደመጀመሪያው በወጣትነት፡ በተሻለ ሁኔታ ላይ በነበረበት ጊዜ የነበረውን፡ ሌላ ወንድም ዊሌትን ይፈጥራሉ።

43 አንድ ሰው ሀያ-አምስት ዓመት ሲሞላው ከዓይኖቹ በታች፡ ጥቂት ነጠብጣብ እና አንዳንድ ግራጫ ፀጉሮች ሲወጡ፡ ያያል። ያ የሚሆነው፡ ምክንያቱም ሞት ስለጀመረህ ነው። አንድ ቀንም ይመጣና ይወስድሃል። ማንም ሁን ማን፡ ይወስድሃል። ነገር ግን ቀስ በቀስ... እዚህ ጥግ ትገባለህ፡ እግዚአብሔርም ከዚያ ጥግ ያወጣሃል፡ **እዚህም** ጥግ ትገባለህ፡ እዚህ ላይ፡ ሞት ሊያገኝህ ነው፡ ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያገኝሃል። ነገር ግን ከዚያ፡ ሞት ምን ማድረግ ይችላል፡ ሙሉ ክፍያ ይወስዳል፡ ከ... ከዚያም ሞት ማድረግ የሚችለውን ሁሉ ካደረገ በኋላ... እግዚአብሔር ይህንን ሕይወት ሲሰጥህ፡ ምርጥ በተባለው፡ የሃያ-ሦስት ዓመት ገደማ ላይ ስትሆን፡ ወደ ትንሣኤ ስትመጣ ልክ እንደ ቀድሞው ትመለሳለህ ልክ ሀያ-ሦስት ዓመት፡ ሀያ-አምስት ሲሞላህ፡ ሞት ከመምጣቱ በፊት እንደነበርከው ትሆናለህ። ሞት ማድረግ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ይገባባሃል፡ ነገር ግን ልክ እንደነበርከው ትመለሳለህ።

44 አሁን፡ በሰውነታችሁ ውስጥ ያ—ያሉትን እያንዳንዱን ህዋሶችን፡ እንውሰዳቸው፡ ያደጋችሁት ከህዋስ ህዋስ በኋላ፡ ከህዋስ ህዋስ በኋላ ነው፡ እዚህ በመድረክ ላይ ለይተን ብናስቀምጥ፡ በሰውነትህ ውስጥ ካሉ ከእያንዳንዱ ሴሎች በኋላ፡ አንተ የተጀመርክበት ሚጢጢዬ ዘር አለ፡ በተፈጥሮ ዓይን ሊታይ አይችልም። የሚታየው በማጉያ መነጽር ነው። እኔ የሕይወትን ዘረ መል በማይክሮስኮፕ አይቻለሁ። ደቃቅ ክር ይመስላል። አጀማመሩ ከጀርባ ይጀምራል፡ እንደ ትንሽ ክሮሽ ነው። ይህ የመጀመሪያው ትንሽ ህዋስ በህዋሱ እናት ላይ ይሰበሰባል።

45 አሁን፡ እያንዳንዳችሁ የተወለዳችሁበትን አንድ ትንሽ ህዋስ፡ ደቃቁ ትንሽ ህዋስ፡ ዘሩን ብወስድ... ዘር ምንድን ነው? ዘር እጅግ ደቃቅ፡ ትንሹ ሕዋስ ነው። መልካም፡ ከዚያ በኋላስ? አሁን፡ ከእናንተ እያንዳንዱ ነገራችሁን እስከ ትንሽ ሕዋስ፡ እስከመጨረሻው ብወስድ፡ ገና አላገኛችሁም። ሴሎቻችሁን ከፈትኩ። እና፡ ከዚያም፡ በመቀጠል፡ የደም ሴሎች፡ የሥጋ ሴሎች፡ እና ምንም ይሁን ምን እነዚህ፡ ሁሉንም ውጭ አውጥቼ፡ እናንተን ገና አላገኛችሁም። አሁን፡ ወደ

አንድ ዘር ወርጃለሁ። መልካም፡ አሁን ያንን ትንሽ ሕዋስ ከፈልኩት። አሁን፡ የት ናችሁ? ሕይወታችሁ። ሕይወትም የመጀመሪያውን ህዋስ፡ ማለትም ዘር ይሠራል፡ ከዚያም ሁሉም ነገር እንደ ተፈጥሮው ይሠራል፥ ውሻ ከውሻ፡ ወፍ ከወፍ፡ ሰው ከሰው። ሕዋሳትን ማዳበር፡ ሕዋስ በሕዋስ ላይ፡ ሕዋስ በሕዋስ ላይ፡ አንተ ወዳለህበት ይመጣል፡ የሰው ልጅ ወደመሆን፡ ሕዋሶች ይዳብራሉ። አሁን፡ ይህ እንዲህ እንዲሆን የወሰነው እግዚአብሔር ነው።

46 ነገር ግን፡ አሁን፡ ካንሰርስ? ሰለ እሱ ትንሽ እንነጋገር። አሁን፡ እግዚአብሔር ሕይወት ሰጣችሁ። እንበልና፡ ዛሬ እዚህ ናችሁ፡ እኔም እዚህ ነኝ፡ በ—በእጄ ምንም ነገር የሌብኝም፡ በአንድ ወቅት ግን በእጄ ላይ ካንሰር ሊኖር ይችላል። መልካም፡ ካንሰሩ እንዴት ሊመጣ ቻለ? እስቲ ካንሰር ምን እንደሆነ እንመልከት፡ እሰኪ ከፍለን፡ እንውሰደው። አሁን፡ እሱም፡ የሕዋሶች ሰብሰብ ነው። ይህን ታውቁታላችሁ? ቲዩመር፡ ካታራክት፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሕዋሶች ናቸው። ቅርጽ የላቸውም። አንዳንዶቹ ይሰፋፋሉ፡ አንዳንዶቹ ደግሞ እንደ ሸረሪት ይመሰላሉ፡ እንዳንዶቹ ደግሞ... እንደ ረዥም ቀይ ክሮች፡ ቅጥልጣይ ቀይ ካንሰር፡ ከ... ከዛም የርዝ ካንሰር አለ ይህም በአብዛኛው የሚመጣው በሴቶች ጡት ላይ ነው፡ እንደ ፓንኬክ አንዱ ሌላውን ይሸፍናል፡ ከዚያም ይሰፋፋል። በየትኛውም ቦታ ያድጋሉ።

47 አንዳንድ ጊዜ እጢዎች ጐን ለጐን፡ **በዚህ** መንገድ፡ ረዥም፡ ሞላላ፡ ሁሉንም ነገር ናቸው። ቅርጽ የላቸውም፡ ምክንያቱም ቅርጽ የሌለውን መንፈስ ይከተላሉና። ይሁን እንጂ የሕዋሶች እድገት ነው። የሕዋሶች ሰብሰብ ነው፡ ለምሳሌ፡ እሁኑ በሰውነታችሁ ውሰጥ ካንሰር ወይም እጢ አለ እንበል፡ አዳጊ ሕዋስ፡ እያደገ፡ እያደገ፡ እያደገ ነው። ህይወታችሁን እየበላ፡ እየመጠጠ ነው። በደም ዝውውር ውሰጥ ይኖራል። የዓይን ሞራ ግርዶሽ ጭጋግ ይይዛል በላዩ ላይ ያድጋል፡ ራሱን ይሸፍናል፡ ዓይኖቻችሁን ያጠፋል። እንዳንዶቹ ይመጣሉ ከዚያም... እንደ ቲቢ በሽታ፡ በትንሽ ትናንሽ ጀርም ብቻ ይመጣል። በመጠን የሚመሳሰለው ምንም ነገር የለም። ይህን የሚያክል መጠን ያለው ጀርም ግን ዝሆንን፡ የሳር ትል—ያሰመስለዋል። አያችሁ? ከጀርም መጠን ጋር የሚነጻጸር የለም።

48 እንዳንዶቹም የሰውነትን ቅርጽ ይይዛሉ፡ እንዳንዶቹ በጭራሽ አይዙም። እንዳንዶቹ በጭራሽ ወደ ሴሎች አይገቡም። እንዳንዶቹ መንፈስ ይሆናሉ፡ ነፍስን ያሠቃያሉ። ያንን ክፍል ለማግኘት እንሞክራለን፡ ያንን ክፍል ለነገ ከሰዓት በኋላ እተወዋለሁ፡ ከቻልኩ፡ ያ የነፍስ-መንፈስ ከየት እንደሚመጣ፡ እና እንዴት **ከዚህ** በታች እንደሚመጣ ነገ እናያለን።

49 አሁንም፡ ጓደኞቼ፡ ይህንን የምናገረው ከሥነ ልቦና አንጻር አይደለም። ከአጋንንት ጋር ለዓመታት ተታግያለሁ፡ እናንተም ታውቃላችሁ። ነገሩን ብታውቁት ኖሮ፡ በሌሊት ጉባኤው ካለቀ በኋላ፡ የሆነ ነገር ይከሰታል። አታውቁም። እስታውሱ፡ መንፈስን ሰትቃወሙት፡ የምትናገሩትን ነገር ብታውቁ የተሻለ ነው። ዝም ብላችሁ አትጩኹ፡ ምንም ፋይዳ አይኖረውም። በእርግጥ አንድ ጋኔን እናንተ መታዘዝ ባለበት ጊዜ፡ በደንብ ያውቀዋል። ምን ያህል በጮኸ፡ ወይም ምን ያህል ዘይት በቀባ አይደለም። እሱ የሚያውቀው እዚህ ጋር ያለውን ነገር፡ ማለት እውነትን ነው። ኢየሱስም፡ "ውጣ" አለው።

50 አስታውሱ፡ ደቀ መዛሙርቱ ግን እየደበደቡ እና እየጎተቱ፡ እሱን ለማባረር፡ ሁሉንም ነገር ሲያደርጉ ነበር። እርሱንም “ለምንድነው ልናስወጣው ያልቻልነው፡” ጠየቁት?

“ባለማመናችሁ፡ ምክንያት ነው፡” አላቸው።

51 እርሱም “ከእርሱ ውጣ፡” አለው። ልጁ ወደቀ ገጥሞት የማያውቅ ባላንጣ ገጠመው። አያችሁ? አያችሁ? ሰልጣንን ይገነዘባሉ።

52 እዚያን ጳውሎስ አጋንንትን ሲያስወጣ ያዩትን፡ እነዚያን ዙረታም ወጣቶቹን ተመልከቱ። የአንድ ካህን ልጆች ናቸው፡ “እኛም ተመሳሳይ ነገር ማድረግ እንችላለን፡” አሉ። ስለዚህ ወረዱና እንዲህ አሉ፡ “እኛም አጋንንትን ማስወጣት እንችላለን።” የሐዋርያት ሥራ 19። የሚጥል በሽታ ያለበት ሰው ዘንድ ወርደው፡ “በኢየሱስ፡ እናምላችኋለን። ከእሱ ውጡ... ” አሉ፡ ዲያብሎስም፡ “አሁን... ” “... ጳውሎስ በሚሰብከው፡ በኢየሱስ ስም!”

53 ዲያብሎስም “አሁን፡ ኢየሱስን አውቀዋለሁ፡ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ፡ እናንተ ግን እነማን ናችሁ? ” ምን እንደተፈጠረ ታውቃላችሁ። ሰዎቹ ላይ ዘለለ፡ ልብሳቸውን ቀዳደደ፡ እነሱ ራሳቸው አበዱ፡ ወደ ጎዳናው ሮጡ።

54 እነዚያ አጋንንቶች ዛሬም አሉ፡ ስለዚህ ብዙ ወግ አጥባቂነት አለ። ዛሬ ማታም፡ ስለዚህች ቤተክርስቲያን። በዛሬው ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ፡ በመለኮታዊ ፈውስ ዙርያ ብዙ ወግ ማጥበቅ አለ፡ ዝም እንዲሉ መደረግ አለበት። በእውነተኛው ዓላማ ሰድብን የሚያመጣ ይህ ነው። እንዲህ ያለ ከባድ ትግል የሚገጥማችሁ ለዚህ ነው። በዛሬው ጊዜ፡ ሃይማኖት የሚባሉት ብዙ ነገሮች አሉ፡ ዝም ሊሉ ይገባቸዋል። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።] ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ብቻ ናቸው! እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን እንዲህ ያለ ከባድ ትግል እንድታደርግ ያደረጋት ይህ ነው። እኛ ግን አሜሪካ ነን፡ አያችሁ፡ ይህ መሆን ያለበት የግድ ነው። እግዚአብሔር ሰንዴው እንክርዳዱና አሜከላው አብረው እንደሚያድጉ ተናግሯል። ለመንቀል አትሞክሩ። አብረው እንዲያድጉ ፍቀዱላቸው፡ ግን ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ፍሬ የለውም፡ ለምን፡ ሕይወት የለም፡ ምንም ነገር የለውም።

55 አሁን፡ ይህን ሕዋስ ተመልከቱት። ለምሳሌ፡ እንደ ብዙዎቹ ጊዜያት፡ እንበልና፡ ቀይ ካንሰር በአብዛኛው የሚከሰተው በሴት ማኅፀን ውስጥ፡ በሴቶች ቁስል እና በመሳሰሉት ነው። አሁን ያንን፡ እንውሰድ፡ ያ ሰው አሁን፡ በሴሉ ላይ፡ ይህ ካ—ካንሰር አለ። አሁን ካንሰር...

56 ተፈጥሮ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ የመንፈሳዊው ጥላ ናቸው። ይህንን ታውቃላችሁ? ምንም ቢሆኑም፡ በተፈጥሮ ውስጥ ያሉት ሁሉም ነገሮች መንፈሳዊ ጥላ ናቸው።

57 ለምሳሌ፡ በዚህ መንገድ፡ በ—በክርስቶስ አካል ውስጥ ስንወለድ፡ ልደታችንን ለማምጣት የሚያስፈልጉ ሦስት ነገሮች አሉ። እነዚህ ሦስት ነገሮች ክርስቶስ በሞተበት ጊዜ ከሕይወቱ የወጡ ናቸው። ከሥጋው ውስጥ፡ ውኃ፡ ደሙ፡ መንፈሱ ተገኘ። ልክ ነው? ሦስቱ ነገሮች፡ ዳግም ስንወለድ የምናልፋቸው ነገሮች ናቸው፣ መጽደቅ፡ መቀደስ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት። አሁን፡ ያ ሁሉ በአንድ ድርጊት ውስጥ ሊሆን ይችላል። ይሁን... ነገር ግን ሳትቀደሱ ልትጸድቁ ትችላላችሁ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ልታምኑ

እና አሁንም ከእናንተ ጋር ቆሻሻ ልትሸከሙ ትችላላችሁ። ነገር ግን ያለ መንፈስ ቅዱስ በጽድቅ፡ እና በንጽህና በቅዱስ ሕይወት መኖር ትችላላችሁ። አያችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ አንደኛ ዮሐንስ 5፡7 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ "በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸው፡ አብ፡ ወልድና፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እና... አብ፡ ቃል፡ እና መንፈስ ቅዱስ፡" ይህም ወልድ ነበር፡ "እነዚህም ሦስቱ አንድ ናቸው። በምድርም ላይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸው፡ ውኃ፡ ደም፡ እና መንፈስ፡ በአንድ ይስማማሉ።" አንድ አይደሉም፡ ግን በአንድ ይስማማሉ። ወልድ ሳይኖራችሁ አብን ማግኘት አትችሉም፣ መንፈስ ቅዱስ ሳይኖራችሁ ወልድ ሊኖራችሁ አይችልም፡ ምክንያቱም የማይነጣጠሉ ናቸው፡ አንድ ናቸው። ሥላሴ በአንድ ውስጥ ነው።

58 እዚህ አከባቢ አልሰማውም፡ ነገር ግን በመላ አገሪቱ ብዙ ትሰማላችሁ፡ የጴንጤቆስጤ ቡድኖች ውስጥ ታላቅ ነገሮች መካከል አንዱ፡ ያ አንዱ ቀላል ነገር ቀላቅለው ይቸገራሉ። እናም አእምሮአቸውን አንድ ላይ አድርጌ ሁለቱም አንድ ዓይነት ነገር እንደሚያምኑ አረጋግጫለሁ። በመካከላቸው ያለው ሰይጣን ነው፡ ያ ብቻ ነው። ታላቂቱ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን እ-... እነዚህን ትንሽ ነገሮችን፡ ያረጁ ወጎችን ወደ ጎን ብላ በተባረከ በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አንድነት ራሷን ብታዋህድ፡ መነጠቅ ይመጣል። ሰይጣን እንዲህ እንዲበታተኑ ካደረጋቸው ግን፡ ምን ይደረጋል። ይህ የእርሱ ሰራ ነው። እነሱም ተመሳሳይ ነገር ያምናሉ።

አንዱ፡ "መልካም፡ **ይህ** ያ ነው" አለኝ።

59 እኔም፡ "መልካም፡ **ይህ** ያ ከሆነ፡ ያ ደግሞ **ይህ** ነው" አልኩት። ስለዚህ ይኸው ነው። ስለዚህ፡ ሁሉም ያው ነው። በእግዚአብሔር ሶስታዊ አንድነት ውስጥ ግን፡ ይኸው ነው። አሁን፡ አሁን፡ እግዚአብሔር በአንድነቱ። እግዚአብሔር አብ፡ ወልድ፡ እና መንፈስ ቅዱስ። አሁን እኛ፡ እንደ አረማውያን፡ "አማልክቶቻችን" አንልም። እሱ "አምላካችን" ነው። አያችሁ? ሦስት መአዝናዊ አምላክ ነው።

60 አሁን፡ ሰይጣንም፡ ሰላሴአዊ መሆኑን አስተውሉ። ኃይሉም በሥላሴ አሰራር እንዳለ ልብ በሉ።

61 አሁን፡ ግን ውኃ፡ ደም እና መንፈስ አዲስ ልደት ሲፈጥሩ ልብ በሉ። ልክ ነው? አሁን ተከታተሉ። አዲሱን ልደት የሚወክለው ይህን ነው። አዲስ ልደት ከመምጣቱ በፊት የተፈጥሮ ልደት ምን ያመለክታል? እ... እናቶች ሆይ፡ ሕፃን ሲወለድ፡ የመጀመሪያው ነገር ምንድን ነው? ውሃ። ቀጣዩ፡ ደም። ቀጣዩ፡ አያችሁ፡ ይህም ሕይወት ይፈጥራል፡ አያችሁ፡ ሰው ይፈጥራል። ውኃ፡ ደም፡ መንፈስ።

62 አሁን፡ ካንሠር፡ ከዚህ በመቀጠል በዚህ ጉዳይ እንነጋገራለን፡ ይመስለኛል፡ አምስት ደቂቃ ገደማ ይቀረናል፡ ለቀጣዮቹ አምስት ደቂቃዎች፡ በካንሠር ላይ እንነጋገራለን። ይህ አካል ማን ነው? ምንን ይወክላል? ስጋን የሚበላ ነው። የሞቱ ነገሮችን የሚበላ፡ አሞራን ይወክላል። በአብዛኛው ጊዜ የካንሠር አጀማመር፡ አንድ ሴል ከተመታ እና ከ—ከተሰበረ፡ ከመቁሰል ነው። እና በዚያ ውስጥ አንዱ ሕዋስ ባክ ያደርጋል። ኦህ፡ ይህ ለባፒትስቶች ትልቅ ቃል ነው፡

አይደል? መልካም፡ ያ ሕዋስ፡ ባክ ያደርጋል። እኔ ራሴ ባክ በማድረግ የሚያምን ባፕቲሰት ነኛና።

63 በቀደም፡ አንድ ሰው፡ በአርካንሳስ ስብሰባ ላይ እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡” አለ... የናዝሪኖች ወገን ነው። ሰውየው ከዛ በፊት ተፈውሶ ነበር። ተፈውሷል... ክራንቾቹን በትከሻው ላይ አድርጎ፡ በከተማው ላይ ይራመዳል። እንዲህ አለኝ፡ “ታውቃለህ? ” አለኝ፡ “በመጀመሪያ ወደዚህ ሰመጣ፡” አለኝ፡ “አንተ... ሰትሰብክ ሰ—ሰምቼ፡ ናዝሪን ነህ ብዬ አሰብኩ።” አለኝም፡ “ከዚያም አብዛኞቹ ሰዎች የጴንጤቆሰጤ እምነት ተከታዮች እንደሆኑ አየሁ፡ አንድ ሰው አንተም የጴንጤቆሰጤ እምነት ተከታይ እንደነበርክ ነገረኝ። አሁን ደግሞ ባፕቲሰት እንደሆንክ ትናገራለህ።” አለኝ፡ “አልገባኝም” አለኝ።

64 እኔም “ኦህ፡ ያ ቀላል ነው፡” አልኩት። “እኔ ጴንጤቆሰጤአዊ ናዝሪን ባፕቲሰት ነኝ፡” አልኩት። ሰለዚህ—እውነቱ ይህ ነው። እሺ። ኖ፡ በመንፈሰ ቅዱሰ አማካኝነት፡ በክርሰቶሰ ኢየሱሰ አንድ ነን። በትክክል።

65 አሁን፡ ልብ በሉ፡ ይህች ትንሽ ሕዋሰ ሰትጎዳ ባክ ታደርጋለች። በሰሱ ይጀምራል። ሌሎች ትናንሽ የሕዋሰ ዘሮች ሕይወታቸውን ለመሰጠት ይሯሯጣሉ። መግል በቁሰል ውሰጥ የሚመጣው በዚያ ነው። እነዚህ እጅግ ሚጢጢ ሰራዊቶች ሰለ ሕይወታችሁ ይዋጋሉ። ወደዚያ እየሮጡ—መርዙን ይመታሉ፡ በዚያ ለመሰብሰብ—የሚሞክሩ የአጋንንት ኃይሎችን ለመምታት፡ ሕይወታቸውን ይገብራሉ። ይህ እንዲሆን... የሚያደርጉት... እጅግ ብዙ የሞቱ ሚጢጢ ወታደሮች ናቸው፡ በደማችሁ ውሰጥ ያለው መግል... በቁሰሉ—ውሰጥ ያለው መግል፡ እናንተን ለማዳንም ሕይወታቸውን የሰጡ ሕዋሶች ናቸው።

66 አሁን፡ አንዲት ሕዋሰ እዚያ ውሰጥ በትክክል መሰራት ካቆመች ይህ ጋኔን ይጀምራል፡ ማደግ ይጀምራል፡ ሴሎችን ማባዛት ይጀምራል። ልጆቻችሁ በማህፀናችሁ እናንተም በእናታችሁ ማኅፀን ውሰጥ እንደምታድጉ፡ እርሱም አካል መሰራት ይጀምራል። ሕዋሰ በህዋሰ ላይ፡ ሕዋሰ በህዋሰ ላይ፡ ሕዋሰ በህዋሰ ላይ፡ በማንኛውም መንገድ፡ በየትኛውም ቦታ፣ ልክ፡ እንደ ሰው ተፈጥሮ፡ ምንም ዓይነት ቅርጽ የላቸውም። ከመንፈሰ የሆነ ነገር ነው። በማንኛውም መንገድ ያድጋል፡ እና ሕዋሰ በሕዋሰ ላይ፡ ሕዋሰ በሕዋሰ ላይ ይጀምራል።

67 እና፡ መጀመሪያ የሚገጥማችሁ ነገር፡ መድከም እና መታመም ትጀምራላችሁ። ወደ ሐኪሙ ሄደህ ምርመራ ያደርግላችኋል። ምናልባት ላያገኘው ይችላል። የሚያገኘው ከሆነ፡ ምናልባት ይቈርጠዋል። በሰርዓት መቁረጥ ከቻለ፡ መልካም፡ አግኝቶታል። ነገር ግን በሰርዓት መቍረጥ ካልቻለ፡ ይህም በአንገት ውሰጥ ወይም በትክክል መቆረጥ በሚቻልበት ቦታ ካልሆነ፡ ከእሱ አንዲት ቅንጣት መኖር ትቀጥላለች። አያችሁ፡ ምክንያቱም እጃችሁን ቆርጣችሁ እንደምታሰተካክሉት፡ ወይም ሌላ ነገር፡ ወይም እንደምትቆርጡት አይደለም... ምን ማለቴ ነው፡ ዋናውን አካል ቆርጣችሁ፡ እጃችሁን ብትተዉ፡ ለምን፡ አይኖርም። ነገር—ግን፡ አያችሁ፡ እንደ እናንተ የሕይወት ቅርጽ የለውም። ይህ የሚንቀሳቀሰ የአጋንንት ኃይል ነው።

68 አሁንም ልብ በሉ፡ እናንተ ሰትጠሩት፡ ዶክተሩም ሲጠራው፡ “ካንሠር” ይለዋል። እግዚአብሔር ግን “ዲያቢሎሰ” ብሎ ይጠራዋል። ተመልከቱ ዛሬ

ላይ። እነርሱ ናቸው የሰጡት... **ካንሰር** የሚለው ቃል የመጣው ከየት ነው? የመጣው ከ... ከላቲን ቃል ሲሆን ይህም በህክምናው ቃል ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን፡ ትርጉሙም “ጊንጥ” ማለት ነው፡ በባሕር ዳርቻ ላይ የሚታዩአቸው ጊንጦች ሁሉ፡ እግሮች ያሏቸው። ካንሰር የ—ሚሰራጨው፡ ሁሉንም ቦታ የሚደርሰው፡ በዚህ መንገድ ነው። **ካንሠር** የሚለው ቃል “ጊንጥ” ማለት ነው። እና ወደ ውስጥ ገብቶ ልክ እንደ ኦክቶፐስ ወይም እንደ ሌላ ነገር እየሄደ፡ ደም ይመጣል። ለምን፡ ቱመር፡ ካታራክት፡ እና ሌሎች በሽታዎች፡ እያንዳንዳቸው ሕይወት ካለው ሴል የመጡ ናቸው፡ ያም ጀርም ደግሞ አካል መሆን አለበት። አካልም ከመሆኑ በፊት፡ ሕይወት መሆን አለበት። ሕዋስ ከመፍጠሩ ወይም ሕይወት ከ—ከመዝራቱ ተጨማሪ ሕዋሶች ከመፍጠሩ በፊት፡ ሕይወት መሆን አለበት። ልክ ነው? አሁን፡ ካንሠር የመጣው ከየት ነው? ማነው፡ ከየት ነው የመጣው? ይህ ከተወሰነ ጊዜ በፊት በእናንተ ላይ አልነበረም፡ ነገር ግን አሁን ምናልባት በእናንተ ላይ ነው። ከየት ነው የመጣው? በውስጣችሁ የሚኖረው፡ ከእናንተ ሕይወት የተለየ ሌላ ሕይወት ነው። ህይወታችሁንም የሚጎዳ፡ የሚያሰቃይ ነው። ኢየሱስም “ዲያብሎስ” ብሎ የጠራው ለዚህ ነው።

69 በዛሬው የሚጥል በሽታ፡ እንዲህ ብለው ይጠሩታል፡ “ኤፒሌፕሲ።” ለምን፡ ኤፒሌፕሲ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ኢየሱስ “ዲያብሎስ” ብሎ ጠርቶታል። ሰውየው ልጁን ይዞ ሲመጣ መሬት ላይ ወድቆ፡ በአፉ ላይ አረፋ የደፈቀበትና፡ የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ ሲሆኑ፡ እርሱ እንዲህ አለ፡ “ጋኔን አለበት፡ ብዙ ጊዜም ወደ እሳትና፡ ወደ ውኃ ይጥለዋል” አለ።

70 አሁን ሰሙን አሻሽለው ኤፕለፕሲ ብለውታል፡ ግን እሱ ዲያብሎስ ነው። ኢየሱስም፡ “አንተ ዲያብሎስ ከዚህ ልጅ ውጣ!” አለው፡ በትክክል። አሁን፡ የሚጥል በሽታ በአብዛኛው የሚከሰተው በኩላሊት ችግር ምክንያት ነው። ምናልባት ትንሽ ጊዜ በዚህ ህመም ወደዚያ ልትገቡ ትችላላችሁ። አያችሁ? የኩላሊት ችግር፡ የሚጥል በሽታ ያስከትላል።

71 አሁን፡ በዚህ ውስጥ ልብ በሉ፡ ከዚያ ያ ሕዋስ እዚያ ይቀመጣል፡ ያ ዲያቢሎስ ነው። ሕይወቱን እየገነባ ነው፣ እያደገ ነው፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠነከረ ይሄዳል። ይህን ለማድረግ አንድ ግዴታ ተቀብሏል፡ እሱም፡ ሕይወታችሁን መውሰድ ነው። ለዚያም ነው ዲያብሎስ የላከው፡ ዕድሜያችሁን ከሰባ እንዲያሳጥር ነው።

72 አሁን፡ ለሁሉም ዶክተሮች ሰላምታዬን አቀርባለሁ። አዎ፡ ወዳጄ። እያንዳንዱን የህክምናን ሳይንስ፡ እግዚአብሔር ለሰዎች ላደረጉት እርዳታ ይባርካቸው። ያ ትክክል ነው። ያለሱ ዛሬ በዓለም ላይ ምን ታደርጉ ነበር? ለህክምና ሳይንስ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ለመኪናዬ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። እግዚአብሔር ሳይንስ አውቶሞቢል እንዲሰራ፡ ባይፈቅድ ኖሮ እስከዚህ ድረስ መራመድ ይከብደኛ ነበር። ለኤሌክትሪክ መብራቶች፡ እጆቼንም ለማጠብ ሳሙና፡ ጥርሶቼንም ለማጽዳት የጥርስ ሳሙና፡ በእርግጠኝነት። መልካም ነገር ሁሉ፡ ከእግዚአብሔር ነውና ስለ ሁሉ አመሰግነዋለሁ።

73 ይሁን እንጂ አንድ ነገር ልንገራችሁ፡ አንድም መድኃኒት ማንኛውንም አይነት በሽታ ፈውሶ አያውቁም። አንዳንድ አጭበርባሪ እኔ ፈውሻያለው

ከሚለው በስተቀር፡ አንድም ዶክተር አይፈውስም፡ ግን እውነተኛ ዶክተሮች ፈዋሽ እንደሆኑ አይናገሩም። በ ሜዮ ብራዘርስ፡ ብዙዎቻችሁን... ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ፡ ቃለ መጠይቅ ተደርግያለው። ከዛ የሚመጡ ሕመምተኞች፡ ህክምና የማይገኝላቸው ናቸው... **የሪደሪስ ዳይጀስት** ጋዜጣ፡ የታሕሳስ ዕትም አንብባችኋል? **የሪደሪስ ዳይጀስት** ጋዜጣ ላይ፡ የወጣውን ጽሑፌን፡ ስንቶቻችሁ ናችሁ ያነበባችሁት? አያችሁ? እነርሱም አትፈወስም ብለው ተሰፋ ስለቆረጡባት ልጅ ቃል መጠየቅ፡ እዚያ ጠሩኝ። እንዲህ ተብሎ ነበር፡ "ይህ የማይቻል ነገር ነው።" ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ተናገረኝና እንዴት እንደሚሆን ነገረኝ፡ እናም ተፈጸመ። መልካም። አሁን፡ ወደዚያ ጠሩኝ። እና ጂሚ እና ሌሎቹ፡ እነ ማዮ የነበሩበት በር ላይ፡ እንዲህ የሚል አንድ ትልቅ ምልክት አለ፡ "ፈዋሾች ነን አንልም። ተፈጥሮን ለመርዳት ብቻ እንናገራለን። አንድ ፈዋሽ አለ፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው።" በዓለም አቀፍ ደረጃ ምርጦቹ ናቸው። አሁን፡ እርግጥ ነው፡ አንዳንድ የማይረቡም አሉ። ያ ትክክል ነው። ደግሞም፡ አንዳንድ አጭበርባሪ ሰባኪዎችም አሉን። መልካም። ስለዚህ፡ በሁለቱም በኩል ይሄዳል።

74 ልብ በሉ፡ ግን ፈዋሽ ነኝ የሚል ማንኛውም ሰው፡ እሱ ተረት ተረት ነው፡ ምክንያቱም ይህን ማድረግ አይችልም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ፡ "ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ ጌታ እኔ ነኝ" ይላል።

75 ጥናቶችን አድርጌያለሁ። እና ወደ ክፍሌም፡ ከ... ከመላው ሃገራት ካሉት ሁሉ የተሻሉ ዶክተሮች መጥተዋል። ወዳጄ፡ የሆነውን ለማወቅ፡ በአደባባይ የማልናገረውን፡ የህይወትን ጀርባ አታውቅም። ሰዎች በሰውር ይመጣሉ። እና በዓለም ላይ ብዙ ኒቆዲሞሶች ገና የሉም ብላችሁ አታስቡ፡ በእርግጠኝነት፡ በሺዎች የሚቈጠሩ አሉ። ይህን ተመልክተው ወደ ሰብሰባው ይመጣሉ። ቲ-ሸርት፡ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ለብሰው ቁጭ ይላሉ፡ በጣም በምትደነቁባቸው ታዋቂ ሰዎች ሰም፡ በሰብሰባው ውስጥ በትክክል ይቀመጣሉ። በጥቂት ቀናት ውስጥ በሰውር በመደወል፡ ቃለ መጠይቅ ለማግኘት ሰው ይልካሉ። አሁንም እንዲህ ይላሉ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እውነት እንደሆነ አምናለሁ፡" ይላሉ። እንደ እኛ ሰዎች ናቸው። በትክክል። እያንዳንዱ ሰው አንድ ቀን ተሻግረን የምንሄድባትን ከጨለማ መጋረጃ ባሻገር ያለችውን ማየት ይፈልጋሉ።

76 እነዚህ ካንሰሮችና እነዚህ ነገሮች ግን በትክክል በሥጋ አካል ውስጥ የተዋቀሩ፡ ወደ ላይ እየገሰገሱ፡ ሕይወታችሁን ያሚወስዱ አጋንንት ናቸው።

77 አሁን፡ እንደ ዶክተሩ ማድረግ ብችል ኖሮ፡ መቍረጥ ብችል፡ ቆርጬም መሬት ላይ መጣል ብችል ኖሮ... ወይም፡ ለምሳሌ፡ እንዲህ፡ እንበልና፡ እናንተ ራሳችሁ፡ በዚህ ምድር ላይ፡ ካንሰር ናችሁ እንበል። አሁን፡ ይሄው መለኮታዊ ፈውስ አለላችሁ። ዶክተሩ እንደሚያድፈርገው እናንተ ማጥፋት ካለብኝ፡ ሰ... ሰውነታችሁ ከምድር እስኪጠፋ ድረስ፡ ሰውነታችሁን ማሸት፡ ወይም ሌላ ነገር ማድረግ አለብኝ። ዶክተሩ እድገቱን እንደሚያጠፋ ሁሉ፡ ከእንግዲህ ምንም ባልተገኙ ነበር። በመለኮታዊ ፈውስ መልኩ ግን፡ እናንተ ካንሠር ብትሆኑ ኖሮ፡ ከእናንተ ውስጥ ሕይወታችሁን ጠርቼ አወጣት ነበር፡ እናንተም በቀጠላችሁ ነበር። ሕይወታችሁ ትቷችሁ ይሄዳል፡ ሰጋችሁ ግን እንደነበረው እዚህ ይቆያል።

78 አሁን፡ በመለኰታዊ ፈውስ ውስጥ የእግዚአብሔር ክፉ ጠላት እይታ

እና ጊዜ ነው። ወንድም ባክስተር በስብሰባው ላይ እነዚህን ነገሮች ይደርስ እንደሆነ አላውቅም። እኔ ቁጭ ብዬ ለእርሱና ለወንድም ቦሰዎርዝ፡ ደጋግሜ አብራርቼላቸዋለሁ። ግን የሆነው ይህ ነው። ብዙ ሰዎች እንደተረዱት እጠራጠራለሁ፡ ምክንያቱም፡ ከጊዜ በኋላ፡ ሰዎች ተመልሰው ሲመጡ ማየት ትጀምራለህ፡ እንዲህ ይላሉ፡ “ፈውስ አግኝቻለሁ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ለሁለት ወይም ለሦስት ቀናት፡ ግን፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡ ት—ትቶኛል።” እኔም አወኩት፡ እናም ስብሰባውን በትክክል ስለማያዘጋጁት ይመስለኛል። ሰዎች አይረዱም። ሰዎች ወደ መድረኩ ሲመጡ ሙሉ በሙሉ ዓይነ ስውር፡ ካንሰር፡ ወይም የዓይን ሽፍታ ያለባቸው ሲሆኑ፡ ይህን መጽሐፍ ቅዱስ ከጸሎት በኋላ ሲያነቡ ተመልክቻለሁ፡ ይሄዱና፣ በሦስት ወይም በአራት ቀናት ውስጥ ልክ እንደ መጀመሪያው ዕውር ይሆናሉ። ምን ይፈጠራል? ማንኛውም ሰው እንደሚያውቀው ሕይወት ከማንኛውም ሥጋ በወጣ ጊዜ፡ ለተወሰነ ጊዜ ሰጋው ይነትባል። ይህ ትክክል ነው?

79 እዚህ፡ አጋዘን፡ ወይም፡ ላም፡ ገድሎ የሚያውቅ ሰው አለ? እርግጥ ነው። መልካም። ዛሬ ማታ ትመዝኑታላችሁ፡ እናንተ እዚህ ያላችሁ አዳኞች፡ ጓደኞቼ። አጋዘን ገድላችሁ ሚዛኑ ላይ አርጉትና ምን ያህል እንደሚመዝን፡ ለሌሎቹ ንገሯቸው። ተመልከቱ! በነጋታው መጀመሪያ ከነበረው ፓውንድ ብዙ ይቀንሳል። አንድ ሰው ሲሞት፡ ቀብር አስፈጻሚው፡ በመጀመሪያ፡ አርተፊሻል ጥርሱን ወይም ዓይኑን ይወስዳል፡ በውስጡ ያለው ምንም ይሁን ምን፡ ያወጣዋል፡ ምክንያቱም፡ እየቀነሰ ይሄዳል፡ ምክንያቱም የሰው አካል እየቀነሰ ይሄዳል። እያንዳንዱ ሌላ ሥጋ ይቀንሳል። ሕይወት ከሕዋሱ ሲወጣ፡ ወደታች መውረድ ይጀምራል፡ ይቀንሳል። ይህ ለሰባ-ሁለት ሰዓታት ያህል ይህን ያደርጋል። ከዚያም መቦርቦር ይጀምራል። ለምሳሌ አንድ ውሻ፡ መንገድ ላይ ተገጭቶ ይሞታል። ለሦስት ቀናት ያህል ፀሐይ ላይ እንዲተኛ አድርጉትና፡ ምን እንደሚፈጠር ተመልከቱ። ከመቼውም ጊዜ በላይ ትልቅ ውሻ ይሆናል። ያብጣል። ይህ ትክክል ነው?

80 እንግዲህ፡ ጋኔን ከ—ከታመመ ሰው ሲወጣም ተመሳሳይ ነገር ይከሰታል። የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ላይ፡ “ኦህ፡ በጣም ጥሩ ስሜት ተሰማኝ።” ከዚያም “ከ—መቼውም ጊዜ በበለጠ ታ—መምኩኝ። ፈውሴን ጥያለሁ፡” ማለት ትጀምራለህ። እምነት አውጥቶ እንደጣለው ሁሉ፡ አለማመንም መልሶ ያመጣዋል። እምነት እንደሚገድለው ሁሉ፡ አለማመን ደግሞ ያነሳዋል። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “ርኩስ መንፈስ ከሰው ሲወጣ፡ በደረቅ ስፍራዎች ይንከራተታል ከዚያም ከሌሎች ሰባት አጋንንት ጋር ይመለሣል።” የቤቱ ጠባቂ በር ላይ ቆሞ ካልጠበቀ በቀር፡ በቀጥታ ወደ ውስጥ ይገባል። የቤትህ ጥሩ ጠባቂ ደግሞ እምነታችሁ ነው። “ዞር በል ከዚህ!” ይለዋል፡ በቃ።

81 አሁን ግን አንድ ታካሚ በተለምዶ፡ ሲፈወስ ትመለከታላችሁ፡ ተአምር ካልሆነ በስተቀር። ሁለቱ፡ መለኮታዊ ፈውስ እና ተአምር ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። መለኮታዊ ፈውስ፡ አንድ ነገር ነው፡ ተአምር ደግሞ ሌላ ነገር ነው። የተለመደው መለኮታዊ ፈውስ ግን፡ ርኩስ መንፈስ ሲባረር፡ የካንሰር ዲያብሎስ፡ ሰውየውን ሲተወው ነው፡ “ኦህ!” አሁን፡ ወይም የበለጠ በምስላዊ እንድታዩት አንድ ነገር እንወሰዳለን፥ ለምሳሌ፡ የሞራ ግርዶሽ። እንዲህ አይነቱ ሰው ሲያጋጥም… ማየት የተሳነው ሰው ልብ ካላችሁት። እኔ የአይን ሞራ ግርዶሽ ያለው ሰው እዚህ አጋጥሞኝ ይሁን፡ አይሁን፡ ገና አላውቅም።

ለጥቂት ደቂቃዎች እንዲቆሙ አደርጋቸዋለሁ። ለምን? መቀነስ እንዲጀምር ነው። ተመልሰው መጥተው፡ ምስክርነት እንዲሰጡን እነጋርቸዋለሁ። "ኦህ፡ ማይ!" በሚደንቅ ሁኔታ ማየት ይችላሉ። "ኦህ፡ ማይ! በቃ፡ ነገሮችን ማየት እችላለሁ! እዋ! እኔ... " ምን ተፈጠረ? ሕይወት ጠፋ፥ የአይን ሞራ ግርዶሽ እየቀነሰ ነው። መልካም፡ ለጥቂት ቀናት ባለበት ይቀጥላል። "እህ፡ በጣም እየተሻለኝ ነው፡" ትላላችሁ።

82 ከጥቂትም ጊዜ በኋላ፡ ራስ ምታት መታመም ይጀምራሉ፡ ጥሩ ስሜት አይሰማቸውም። በማግሥቱ ጠዋት ሲነቁ "እንደገና ዓይኔን እያጣሁ ነው፡" ይላሉ።

83 አንዳንዶች "ወይ-ጉድ፡ ተታለሃል። እነዚያ ወንበር-ሰባሪዎች አታለውሃል፡" ይሏቸዋል። ይህን አትመኑ! ይህ የዲያብሎስ ውሸት ነው። ይህን ካመናችሁ፡ ወደኋላ ተመልሳችሁ ዕውር ትሆናላችሁ።

ነገር ግን ወደ ኋላ ጠበቅ አድርጋችሁ፡ እንዲህ በሉ፡ "አይ። ጌታ ሆይ፡ እኔ አምናለሁ።"

84 ከዚያም ምን ይሆናል? ይህ አካል ለረጅም ጊዜ ያብጣል። ያንን አይን በድጋሚ ይሸፍናል። በሰውነታችሁ ውስጥ ያለው ካንሠር ያብጣል። እንደገና ይጎዳችኋል እና ያማችኋል። ከዚያ በጣም ትታመማላችሁ፡ በጣም ትታመማላችሁ። ለምን? አንድ የሞተ አካል፡ የሞተ ነገር በውስጣችሁ እዚያው ተኝቷል።

85 ወደ ኋላ ተመልሳችሁ፡ ዶክተሩም "ኦህ፡ ትርጉም የለውም። ካንሠሩ ይታየኛል። ማየት እችላለሁ፡" ይላችኋል። እርግጥ ነው፡ አለ፡ ነገር ግን የሞተ ነው። ሃሌሉያ!

86 ስለዚህ፡ የደም ዝውውር ሰውነትን ማጽዳት አለበት። ልብ በሚመታ ጊዜ ሁሉ፡ ደሙን በሰውነት ዙሪያ ይረጫል፡ እናም ኢንፌክሽኑን ያነሳል። እርግጥ ነው፡ እንዲያማችሁ ያደርጋል። የሥጋ ቊራጭ የሆነ ቦታ ላይ ቢንጠለጠል፡ ወይም እንደ እባብ ረዥም፡ ወይም እንደ ጣታችሁ ትልቅ የሆነ ነገር ቢንጠለጠል፡ እዚያም ቢንጠለጠል፡ የሞተ ቢሆንስ፡ ያ ሁሉ የሞተ ሥጋ ቢንጠለጠል፡ እየበሰበሰም ቢሆንስ? እርግጥ ነው፡ የደም ቧንቧችሁ በረጨ ቁጥር፡ ንጹሕ ሆኖ እንዲቆይ፡ ማድረግ አለበት። ነገር ግን አንድ በዚያ የተንጠለጠለ፡ የሞተ አካል አለ፡ ምክንያቱም ሕይወት ከእርሱ ሄዷል። በእምነት አማካኝነት፡ የእግዚአብሔር ኃይል፡ አውጥቶታል። እሱ ጋኔን ነው፣ መውጣት አለበት።

87 የዚህ ሁሉ፡ ምክንያት ግን፡ የሕዝቡ አለመማር ነው። ተስፋ ቆርጠው፡ ይሄዳሉና። ያንኑ ዲያብሎስ እንደገና ድል ለመንሣት፡ በፊታቸው ይቆማል። እግዚአብሔር በዚህ መድረክ ላይ፡ በመንፈሱ አማካኝነት፡ በመንፈስ አነሳሽነት፡ አንድ ነገር ሲነግራችሁ አትጠራጠሩ፡ አለበለዚያ ከዚህ የከፋ ነገር ይመጣባችኋል፡ እርሱ ብሏልና። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ "የዚያ ሰው የኋለኛው ሁኔታ ከቀድሞው ሰባት እጥፍ የከፋ ይሆናል።" ይህ እውነት ነው? ርኩሱ መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ፡ በደረቅ ስፍራዎች ይዞራል፡ ሌሎች ሰባት አጋንንትንም ይዞ ይመለሳል። ስለዚህ፡ አታምኑም። ከእሱ ጋር በትክክል ቆዩ። ከልባችሁ፡ ማለት ነው። እንዲህ በሉ፡ "አይ፡ ወዳጄ! አልንቀሳቀስም! ምንም ያህል ብታመም፡ ያ ከእሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።" ከዚያም፡ መጀመሪያ

የሚታወቃችሁ ነገር፡ ደህና መሆናችሁ ነው። ያኔ ሁሉም ነገር ደህና ይሆናል። እያችሁ፡ ሞቷል። ዶክተሩ ከእናንተ ውስጥ በ—ቀዶ ህክምና የሚያወጣው፡ በውስጡ ሕይወት የሌለውን፡ ያንን ተመሳሳይ እብጠትን ነው።

88 “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ በውስጡ ያለው ያ ሕይወት፡ ሕይወቴን ይወርሰብኛልን፡” ብላችሁ ትጠይቃላችሁ? አይወርሰብህም፡ ወዳጄ። ያ ሕይወት ከእናንተ ሕይወት የተለየ ነው። ሕይወት የነበራችሁ አሁን አካል እንደሆናችሁ አሳይቻችኋለሁ፡ ይህም ሕይወት ነው አካልም ይሆናል። እናንተ የእግዚአብሔር፡ እሱ የዲያብሎስ ነው። ምን ለማለት እንደፈለኩ አይታችኋል? መናፍስታዊነት። አሁን፡ ያ ነገር ቆማችሁ ሲትመለከቱት ምን እንደሚመስል ማየት አለባችሁ።

89 ኦህ፡ ማይ፡ ይቅርታ አድርጉልኝ፡ ሦስት-ተኩል ገደማ ሆኗል። ይቅርታ። ተመልከቱ፡ ወዳጆቼ። ኦህ፡ ይህ ዓለም ምን እንደሚያስፈልገው!

90 እነዚህን የመፈወስ አገልግሎቶችን እያደረግኩ፡ ለሰባት ዓመታት ያህል፡ በመላው አሜሪካ እያስተማርኩ ቆይቻለሁ። በመላ አገሪቱ በጅማሬ ላይ ጥሩ ምላሽ አግኝቼበታለሁ፡ ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው መረዳት እንዲችሉ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ ስለ መናፍስት ትምህርት አስተምሬአለው። ብዙ ጊዜ፡ ወደ እነዚህ ስብሰባዎች የሚሄዱት፡ ለዚህ ነው፡ እና፡ ወዳጅ... ካልገባችሁ፡ ሰዎች ይመጡና፡ ብዙ ጊዜ...

አሁን፡ መለኮታዊ ፈውስ ስጦታ አለኝ ብሎ የተናገረውን ያንን ሰው ታስታውሳላችሁ? ከተፈወሳችሁ መለኰታዊ ፈውስ ስጦታ በእናንተ ውስጥ አለ። እናንተው፡ ራሳችሁ ናችሁ። ማንኛውም ስጦታ የሚሠራው በእምነት ነው። ምንም ያህል መለኰታዊ የመፈወስ ስጦታ ቢኖረኝም፡ በሙሉ ልቤ አምናለሁ፡ እናንተ እዚህ ቆማችሁ ግን፡ ተመሳሳይ ዓይነት እምነት ከሌላችሁ፡ ለምንም አይጠቅምም። ለሰዓታት፡ እና ለሳምንታት እና ለወራት ልጸልይላችሁ እችላለሁ። መለኮታዊ ፈውስ ያላቸው ሰባኪዎቹ አይደሉም። በእምነት ነውና፡ አማኞች በመፈወሳቸው ምክንያት፡ የመለኮታዊ ፈውስ ስጦታ ያለባችሁ እናንተው ናችሁ። በእምነት! የእግዚአብሔር ሥራ ሁሉ በእምነት ነው።

91 የእግዚአብሔር ሙሉ የጦር ትጥቅ በእምነት ነው። ከዚህ ዓለም የተቀበልነው አንድም ተፈጥሯዊ ነገር የለንም። እያንዳንዱ የ—የክርስቲያን ቤተክርስቲያን ተግባር የእምነት ተግባር ነው። የእግዚአብሔርን የጦር ትጥቅ ተመልከቱ፡ ፍቅር፡ ደስታ፡ ሰላም፡ መታገስ፡ ቸርነት፡ የዋህነት፡ ገርነት፡ ትዕግሥት ናቸው። ትክክል ነው? ሁሉም ነገር ከተፈጥሮ በላይ ነው፡ ተፈጥሯዊ የሆነ ነገር የለም። ስለዚህ እኛ በተፈጥሮአዊ ነገሮች ላይ አንመለከትም፡ ምክንያቱም ሂደታችን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ነው። መሰረት የምናደርገው ብቸኛው መንገድ፡ እምነት ነው፡ እግዚአብሔር እውነት ነው ብሎ በተናገረው ላይ ነው፡ የማይታየውንም እንመለከታለንና። አብራሃም አምኖ፡ እንደተቀበለ፥ የሌሉትን ነገሮች፡ እንዳሉ አድርገን እንቆጥራቸዋለን። አሜን! አብርሃም እንደ እግዚአብሔር፡ ያልነበሩትን ነገሮች፡ እንደነበሩ አድርጎ ቆጠራቸው። የመቶ ዓመት አዛውንት ቢሆንም፡ በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ በአለማመን አልተጠራጠረም።

92 ያን ነገር በምናቤ አሰበዋለሁ፡ እናንተስ? ሣራ እዩአት አንድ ቀን ማልዳ ተነሣች። እግዚአብሔር እንዲህ ብሎታል፡ "አብርሃም ሆይ!" "አብርሃም ሆይ፡ ልጅ ትወልዳለህ፡" ብሎት ነበር።

93 ሣራም ተነሳች። ከዛ "ሳራ ሆይ፡ ምን ይሰማሻል፡" ብሎ ይጠይቃታል? ድብልቅ ጉባኤ ነው፡ ግን አዳምጡ።

"ምንም ለውጥ የለም።"

94 "መልካም፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡ እናገኘዋለን! የሕጻን ጨርቅ እና ቁልፎቹን አዘጋጂአቸው። ተዘጋጂ።"

መልካም፡ ሌላ ወር አለፈ። "ሳራ፡ እንዴት እየሆንሽ ነው? "

"ምንም ለውጥ የለም።"

አመት አለፈ። "ሳራ፡ አሁንስ እንዴት ነው? "

"ምንም የተለየ ነገር የለም።"

አሰር አመታት አለፉ። "ምንም ለውጥ የለም።"

ሃያ-አምስት ዓመታት አለፉ። "ምንም ለውጥ የለም።"

95 አብርሃም፡ ከመዳከም ይልቅ፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ ሄደ። እምላክን ያምን ስለነበር በተደጋጋሚ ጊዜያት ተአምር እንደሚፈጸም ያውቅ ነበር፡ እንዲሁም እግዚአብሔር የገባውን፡ ተሰፋ ቃል ባለማመን አላመነመነም። እንዲህ አለ፡ "እናገኘዋለን!" አንድ ቀን ጠዋት የሣራ ማኅፀን ማበጥ ጀመረ፡ አብርሃም በእግዚአብሔር ሰላመነ፡ ትንሹ ይሰሐቅ ተወለደ። ነገሩን ተመለከተና፡ የሌለውን ነገር እንዳለ አድርጎ ቈጠረ።

96 በሰሜት አይደለም፡ በማየት አይደለም። በሰሜት ወይም በማየት አትመላለሱም። በእምነት ነው። እግዚአብሔርም አንድን ነገር በተናገር ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ "የምትለምኑትን ሁሉ፡ በምትጸልዩበት ጊዜ፡ እንደተቀበላችሁት እመኑ፡" ከዚያም በእሱ ጋር ተጣበቁ። እግዚአብሔር እንደዛ ሰላለ፡ እንደዚያ መሆን አለበት! ኣሜን። አጋንንት!

እምነት በአባት ላይ፡ እምነት በልጅ ላይ፡
እምነት በመንፈስ ቅዱስ፡ ሦስት በአንድ ላይ፡
አጋንንት ይንቀጠቀጣሉ ኃጢአተኞችም ይነቃሉ፥
እምነት በጁሆቫ ማንኛውም ነገር ይንቀጠቀጣል።

እውነት ነው። ኦህ፡ ማይ! በእርግጠኝነት ነው። በእግዚአብሔር ላይ እምነት ይኑራችሁ። ወደ እርሱ ተመልከቱ። አትናወጡ። ጸንታችሁ ቁዩ። እግዚአብሔር ተናግሯልና!

97 እና፡ አጋንንት፡ ምንድን ናቸው? መንፈሳዊ ፍጡራን ናቸው። አሁን፡ ዶክተሩ እ—እንዲህ ሲል፡ "ካንሠር አለብህ። ቲቢ አለብህ። ካታራክት አለብህ። ፕሌይራይቲስ አለብህ። **ይሄም** አለብህ።" እሱ ዲያብሎስ ነው። ሕይወት ነው፡ በዚያ ሕይወት በስተጀርባ መንፈስ አለ። ካንሠር፡ የ—የዓይን ሞራ ግርዶሽ፡ መንፈስ መሆኑንና በ—በውስጡ... ሕይወት እንዳለው፡ ሰንቶች ያውቃሉ። እሺ፡ ሕያው የሆነ ነገር ያለ መንፈስ መኖር አይችልም፡ አያችሁ፡ ሰለዚህ ያንን ለማንቀሳቀስ፡ የሆነ ቦታ ላይ ሕይወት መኖር አለበት።

98 ያች ዛፍ እንኳን በውስጧ ሕይወት አላት። የዓለማችን ሳይንስ ሁሉ አንድ የሳር ቅጠል እንኳ ሊሠራ አይችልም። ይህን ታውቃላችሁ? እንዲመስል ያደርጉታል፡ ነገር ግን የሕይወትን ቀመር ማግኘት አይችሉም። ያም እግዚአብሔር ነው። አያችሁ? ኢየሱስ ዛፏን እንዲህ አላት፡ “አንቺ የተረገመሽ ነሽ። ፍሬ የለሽምና፡ ለዘላለምም ፍሬ አይኑርብሽ።” ኋላ ላይ በዚያ በኩል አለፉ። ጠዋት ሁለት ሰዓት ላይ ነበር። እራት ለመብላት ወደ አስራ አንድ ሰዓት ገደማ፡ በዚያ ብኩል ተመለሱ። ጴጥሮስም “ያችን ዛፍ ተመልከቷት፡ ከስር እስከ ላይ ደርቃለች፡” አላቸው። ለምን? ኢየሱስ በዚያ ዛፍ ውስጥ የነበረውን፡ በሥሮቹ ውስጥ የነበረውን ሕይወት ገሠጸው፡ እና ሁሉም ነገር ሞተ። ሃሌ ሉያ!

99 ያው ክርስቶስ ካንሠርን ከሥሩ ሊገሥጽ ይችላል፡ ሁሉም ነገርም ይሞታል። ይህ ዛፍ ከጥቂት ሰዓታት በፊት፡ እንደነበረው ቆሞ ነበር፡ ይሁን እንጂ ቅጠሎቹ መውደቅ ጀመሩ፡ ከዚያም ቅርፊቶቹ መንሸራተት ጀመሩ። እና… ከቀን ወደ ቀን፡ ከሳምንት ወደ ሳምንት፡ እየቀነሰ መምጣት የጀመረ ሲሆን፡ ከጊዜ በኋላ የዛፉ ጉቶ እንኳ አልቀረም። ሃሌሉያ! ካንሠር፡ እጢ፡ ካታራክት፡ ወይም ሌላ ማንኛውም ነገር፡ ክርስቶስ በሚናገርበት ጊዜ ይሄዳል። እርሱ አጋንንቶችን ያወጣል። እርሱም እንዲህ አለ፡ “በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፡ እባቦችን ይይዛሉ፡ ወይም ገዳይ የሆነ ነገር ይጠጣሉ፡ አይጎዳቸውም። እጆቻቸው በበሽተኞች ላይ ቢጭኑ፡ ይፈወሳሉ።”

100 ትወዱታላችሁ ወይ? ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ እዚህ አንድ ሰዓት ተቀምጣችሁ ስለቆየኋችሁ ይቅርታ አድርጉልኝ። ጌታን ትወዱታላችሁ? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] አሁን ምን ሊፈጠር ነው? ክርስቶስን እንደ ፈዋሻችሁ ከተቀብላችሁ፡ በልባችሁ የሆነ ነገር እንደሆነ ካመናችሁ፡ እና እንደተፈወሳችሁ እመኑ፡ እንደተፈወሳችሁ ታምናላችሁ? ዲያብሎስ ሌላ ነገር እንዲሰካባችሁ አትፍቀዱ። ቀጥሉ አታቁሙ።

“ዶክተርን፡” “ዶክተር፡ ምን ይመስልሃል፡” ት—ትላላችሁ?

እርሱም “ያው፡ አሁንም አለ፡” ይላችኋል።

101 በልባችሁ ስለምታውቁ፡ ምን እንደተፈጠረ ታውቃላችሁ። ኸሃ! የመጀመሪያ ማወቅ ያለባችሁ፡ እንዲህ በሉት፡ “በዛ ነገር ላይ የተፈጠረ ነገር ይገርማል፡ አልክ? ”

102 ከዚያም እንዲህ በሉት፡ “ይኸውልህ፡ ዶክተር፡ አንድ ነገር እነግርሃለሁ። የሆነው ይኸው ነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶኛል። በትክክል። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶኛል።”

103 መልካም፡ ለአፍታ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። ወንድም ዊሌት፡ ለአንድ ደቂቃ ወደዚህ ትመጣለህ፡ ወንድሜ?

104 አሁን፡ የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ ለክርስቶስ ደም እናመሰግናለን። ምናልባትም አንዳንድ ጊዜ ባሪያህ፡ ጌታ ሆይ፡ ረጅም ጊዜ በመናገር፡ ጥበብ ይጎድልበታል። እኔ ግን ሌሉቱን ሙሉ ሲሰብክ እንዳደረ፡ እንደ ጳውሎስ ይሰማኛ ይሆናል። አንድ ምስኪን ሰው ከመስኮት ወድቆ ሞተ። ያ ሐዋርያም፡ በሕይወቱ የእግዚአብሔርን ቃል ይዞ፡ ሄዶ ሥጋውን በልጁ ላይ አኖረ፡ ሕይወትም ገባበትና እንደገና ኖረ።

105 አምላክ ሆይ፡ የዚህ ታላቅ ሥልጣኔ የፀሐይ መጥለቅ አሁን እየጠለቀ መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡ ከረጅም ጊዜ በፊት፡ የቀኑ አጋማሽ አልፏል፡ የምሽቱ ጥላዎች እየወደቁ ናቸው። ታላቁ ብርሃን ከአምላክ መንግሥት እየወጣ፡ በምድር ላይ ከሚመጣው ጨለማ ቦታውን ይይዛል። እግዚአብሔር ሆይ፡ በየቀኑ እያረጀው እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ። ልሂድ፡ ጌታ ሆይ። ጥንካሬን ስጠኝ። ይህን ታላቅ እውነት በየቦታው እንድናገር እርዳኝ። ነገ ከሰአት በኋላ፡ የበለጠ ለመረዳት እንድንችል፡ እርዳን።

106 እና፡ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ከሰአት በኋላ ይህን ትንሽ ጉባኤ ባርክ። ዛሬ ማታ፡ ለፈውስ አገልግሎት በሚሰበሰቡ ጊዜ፡ እያንዳንዱ ወንድ እና ሴት እርስ በእርስ ተገናኝተው በመነጋገር ይሂዱ፡ እንዲህ እየተባባሉ፡ “አሁን፡ ከ—ከእንግዲህ... ጥርጣሬ አይኑረን። አሁን ከየት እንደመጣ ተረድተናል። ዲያብሎስ መሆኑን እናውቃለን። ሲሄድም፡ በእግዚአብሔር ትእዛዝ መውጣት እንዳለበት እናውቃለን። ማድረግ አለበት። እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል። መተው አለበት።” ከዚያም፡ ደስተኞች ሆነው፡ ሐሴት እያደረጉ፡ ፈውሳቸውን እየተናገሩ፡ ይውጡ። ምንም ነገር፡ ከእንግዲህ፡ ምንም ነገር በመንገዳቸው ላይ አይቁም፡ በማመን ብቻ፡ ይሂዱ።

107 እና፡ አምላክ ሆይ፡ እዚህ ላይ ይህ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን፡ እና እነዚህ ተባባሪ አብያተ ክርስቲያናት፡ ከዚህ ስብሰባ በኋላ መታደስ ይሁንላቸው፡ ጌታ ሆይ፡ ያ ብቻ ይጨምረዋል፡ ብዙ ነፍሳትም በመቶዎች የሚቈጠሩት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይምጡ። አድርገው፡ አባት ሆይ። እዚህ ያሉ ወንዶችና ሴቶች፡ ከሁሉም ሀገሮችና ከሌሎች ቦታዎች የመጡ፡ መልዕክቱን ወደ ቤተክርስቲያኖቻቸው ይዘው ይሂዱ፡ እናም የመጀመሪያ-የሆነ መነቃቃት ይኑራቸው። አድርገው፡ ጌታ ሆይ። አሁን ኃጢአታችንን ይቅር በለን። አገልጋዮችህ እንድንሆን እርዳን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

108 እዚህ ተቀምጣችሁ ሳላችሁ፡ ዛሬ በዚህ ሕንጻ ውስጥ፡ ኃጢአተኛ የሆነ ሰው፡ እንዲህ የሚል፡ “ወንድም ብራንሃም በጸሎትህ አስበኝ።” የሚል ይኖር ይሆን? እጃችሁ ታነሣላችሁ፡ ታነሣላችሁን? ኃጢአተኛ የሆነ ሰው አለ? እኔ አላውቅም... እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። አለ? እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወዳጄ። አንተ፡ አንተ፡ እና አንተ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።... ከሆነ ብዬ እጠይቃለው አሁን፡ ይህ ለእናንተ ነው።

109 እያችሁ፡ ወደ ጉባኤው ወደኋላ በመሄድ አላምንም። የሚሄዱትንም ደግሞ አልነቅፍም። በጉባኤ ውስጥ ወደኋላ በመሄድ የሆነን ሰው በመጎተት አላምንም። እያችሁ? “አብ ከሳበው በቀር፡ ማንም ሊመጣ አይችልም።” እያችሁ? ያ ትክክል ነው። ያለ ፈቃዱ ትጎትታላችሁ። እያችሁ? እግዚአብሔር ልብህን ቢያንኳኳው ግን፡ አንተ በዓለም ላይ ከሁሉ የላቀ የታደለ ሰው ነህ። ከሰንት ሰዎች ጋር እንደተነጋገርኩ አታውቁም።

53-0608A አጋንንቶች፡ በሥጋዊው አድማስ
ሮበርትስ ፓርክ አምፊቲያትር
ኮነርስቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org